# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 297 ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# የአየር ንብረት ለውጥ

## እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም በልማት እቅዶች ተካትቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው

**ዘላለም ግዛው**



ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት የአየር ንብረት ለውጥ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም በልማት እቅዶች በተገቢና በሚፈለገው መልኩ ተካትቶ ተግባራዊ በማድረግ የኢትዮጵያን ልማት እውን ለማድረግ ትኩረት መስጠቱን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅድ ማስተግበሪያ መርሐ ግብር ትናንት ይፋ በሆነበት መርሐ ግብር የተገኙት አቶ ተመስገን፤ ተጨባጭ ለውጦች ማምጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ወጥተው ተግባራዊ መደረጋቸውን አመልክተዋል፡፡

በፓሪሱ ስምምነት መሠረትም እቅድ መዘጋጀቱን፣ የቀጣዮቹን 30 ዓመታት የኢትዮጵያን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስልት የሚያመለክት ስትራቴጂ መኖሩንና አነስተኛ የካርበን ልቀት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ እድገት ስትራቴጂ መተግበሩንም አቶ ተመስገን አስታውሰዋል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያና የአረንጓዴ ልማት ማሳኪያ ተጨባጭ ርምጃ

የአየር ንብረት ለውጥ.. ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# በኢትዮጵያ

## አንድ ተሽከርካሪ በአማካኝ ከመቶ በላይ ዜጎችን እያገለገለ ነው

- ኢትዮ አውቶሞቲቭ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኤክስፖ ትላንት ተከፍቷል

ገጽ 4



ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሤ

# ንቅናቄው ሕገወጥነትን በመከላከል የገቢ አሰባሰብን ለማሳደግ አስችሏል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ የታክስና የጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ንቅናቄ ሕገ-ወጥነትን በመከላከል የገቢ አሰባሰብን ለማሳደግ አስችሏል ሲሉ የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሤ ገለጹ፡፡

"ግብር ለሀገር ክብር" በሚል መሪ ሃሳብ ለአንድ ዓመት ሲካሄድ የቆየው ሀገር አቀፍ የታክስና ጉምሩክ ሕግ

ንቅናቄው ሕገወጥነትን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያውያን የተረጂነት ሥነ-ልቦናን በማሸነፍ የተከበረች ሀገር ለቀጣዩ ትውልድ ሊያስተላልፉ ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን የተረጂነት ሥነ-ልቦና በማሸነፍ ምርታማነቷ የተረጋገጠና የተከበረች ሀገርን ለቀጣዩ ትውልድ ሊያስተላልፉ እንደሚገባ አባ ገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ሀዳ ሲንቄዎች ገለጹ፡፡

የኦሮሞ አባ ገዳ ኅብረት ጸሐፊና የቱለማ አባ ገዳ ጎበና ሆላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የነፃነት ተምሳሌት የሆነች ኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት እየተገዳደረ የሚገኘውን የተረጂነት ችግር ኢትዮጵያውያን ተባብሮ በመሥራት ምርታማነቷ የተረጋገጠና የተከበረች ሀገርን ለቀጣዩ ትውልድ ሊያስተላልፉ ይገባል፡፡

በገዳ ሥርዓት ውስጥ አንድ ሰው በሕይወት ቆይታው እራሱን ለመቻል ምን መደረግ እንዳለበት በግልጽ መቀመጡን ገልጸው ከተረጂነት አስተሳሰብ ለመውጣት የኦሮሞ ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመቀናጀት መሥራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ተረጂነት ክብረነክ መሆኑን የጠቀሱት አባ ገዳ ጎበና ይህም በኢትዮጵያ ባሕል ውስጥ አጸያፊና ነውር የሆነ ተግባር ነው ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያን ፀጋ በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል ባለመቻሉ ተረጂነትና ልመና ልምድ ሆኖ መቀጠሉን ገልጸው ይህም የመሥራት ባሕልን ጎድቶታል ብለዋል።



አባ ገዳ ጎበና ሆላ



አቶ አሕመድ ዘካርያ

ወጣቶች ሀገርን የመለወጥ አቅም እንዳላቸው ተረድተው በተለያዩ የልማት ዘርፎች ሊሠማሩና የሀገርን ብልጽግና ሊያረጋግጡ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከተረጂነት አስተሳሰብ ለመላቀቅ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚገባ ጠቁመው፤ መንግሥት ከተረጂነት ለመላቀቅ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የሀገር ሽማግሌ አቶ አሕመድ ዘካርያ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ተዝቆ የማያልቅ በርካታ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ሀብት ባለቤት መሆኗን ገልጸው እነዚህን ሀብቶች አውጥቶ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አሕመድ ገለጻ፤ በኢንዱስትሪና በቴክኖሎጂ የቀደሙ ሀገራት ኢትዮጵያ ሁሌም የምርታቸው ማራገፊያና ጥገኛ እንድትሆን እየሠሩ መሆናቸውን በመረዳት ትውልዱ ተረጂነትን በቃ ማለት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያውያን የተረጂነት .. ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ አሸናፊ ጉዲታ

አቶ ኦርዲን በድሪ

## ክልሉ በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ አካላት ተጨማሪ ማበረታቻዎችን እንደሚያደርግ አስታወቀ

**አዲሱ ገረመው**

ሐረር፡- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ ዲያስፖራዎችና ኢንቨስተሮች ተጨማሪ ማበረታቻዎችን እንደሚያደርግ የሐረሪ ክልል አስታወቀ።

26ተኛውን ዓለም አቀፍ የሐረር ቀን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው የንግድ ትርኢትና ባዛር በትላንትናው እለት በሐረር ከተማ ተከፍቷል።

የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ 26ተኛውን ዓለም አቀፍ የሐረር ቀን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀውን የንግድ ትርኢትና ባዛር ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር፣ ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ ዲያስፖራዎችን ጨምሮ ኢንቨስተሮችና ባለሀብቶች፣ በክልሉ አሊያም በሀገሪቱ በኢንቨስትመንት ሥራ ተሰማርተው እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል። የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ በተለይም በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ አካላት መሬት በምደባ ማቅረብን ጨምሮ ሌሎች ተጨማሪ ማበረታቻዎች እንደሚደረጉም አስታውቀዋል።

የዘንድሮው 26ተኛው ዓለም አቀፍ የሐረር ቀን የማኅበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከርና ኢኮኖሚውን የበለጠ በማነቃቃት ፈጣን እድገትን ለማስመዝገብ የሚከበር ነው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ በዚህ መነሻነትም የማኅበራዊ መስተጋብርን ከማጠናከር አኳያ በዓሉ ከልዩነት ይልቅ አብሮነትን፣ ከመገፋፋት ይልቅ መደጋገፍን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ እንዳለ ተናግረዋል።

ከዚህም ባሻገር መሰል የንግድ ትርኢትና ባዛር ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት ኢንቨስትመንት በክልሉ የበለጠ እንዲጠናከር ያግዛል በማለት፣ የሥራ ዕድል ተፈጥሮ ወጣቶችና ሴቶች በተለይም በድህነት ጫና ውስጥ ያሉ ወገኖች ገቢ እንዲያገኙና ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ክልላቸውንና ሀገራቸውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ እንደሚሠራ ገልጸዋል።

ኢንዱስትሪዎች ምርትና ምርታማነታቸውን ጨምረው ለሀገሪቷ እድገት የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ የንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲሁም የምርት ማስተዋወቅ መድረክ ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑ ጠቁመዋል።

መድረኩ ሲዘጋጅ በክልሉ በተለይም በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ ኢንቨስተሮችና ባለሃብቶች ክልሉ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ርዕሰ መስተዳድሩ ገልጸዋል።

ዘላቂ ሠላምና የተረጋጋ አካባቢን ለመፍጠር እንዲሁም አሁን ያለውን ሠላምና መረጋጋትን ለማጽናት በቁርጠኝነት እየተሠራ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ሐረር ከአንድ ሺህ ዓመት በላይ ታሪክ ያላት መሆኗን የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ በኢኮኖሚው ሥራዎችና በማኅበራዊ መስተጋብር በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተቸራት ታሪካዊ ሥራዎች የሚሠሩባት እድሜ ጠገብ ከተማ መሆኗን ተናግረዋል።

ሐረር ከምትታወቅባቸው ጉልህ ታሪካዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ ዓለም አቀፍ ንግድ መሆኑን በመጥቀስ፣ በተለይ በበርበራና በዘይላ በኩል የተደረጉ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ሲከወኑባት እንደነበር አንስተዋል።

በሀገር ደረጃም አንድ ሺህ ዓመት ያስቆጠረ የራሷ መገበያያ ገንዘብ የነበራትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ ሁለት ቅርሶችን ማስመዝገብ የቻለች መሆኗንም ገልጸዋል። በመሆኑም በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሐረርን በኢኮኖሚው ዘርፍ በመደገፍ ይበልጥ ማሳደግ እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

በንግድ ባዛሩ አጐራባች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ አስመጪና ላኪዎች እንዲሁም የተለያዩ የንግድ ወኪሎች ተሳትፈዋል።

“ሐረር የሠላም፣ የመቻቻልና የአብሮነት ተምሳሌት” በሚል መሪ ሀሳብ 26ኛው ዓለም አቀፍ የሐረር ቀን ዛሬ ይከበራል።

# ጉባኤው የአዳዲስ ክልሎችን የንግድ ምክር ቤቶች አባልነት እንደሚያፀድቅ ይጠበቃል

**ዓመለወርቅ ከበደ**




አዲስ አበባ፡- በ10ኛው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ በአራት አዳዲስ ክልሎች የተመሠረቱ የንግድ ምክር ቤቶች አባልነት እንደሚያፀድቅ ይጠበቃል።

ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም የሚካሄደውን 10ኛ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ ምክር ቤቱ በትናንትናው እለት መግለጫ ሰጥቷል።

በወቅቱ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት መላኩ እዘዘው (ኢ/ር) እንደተናገሩት፤ አዲስ በተመሠረቱ አራት ክልሎች የንግድ ምክር ቤት እንዲመሠረት የተደረገ ሲሆን፤ በጉባኤው ላይ አባልነታቸው እንዲፀድቅ ይደረጋል።

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በአራት ክልሎች መከፈሉን በማስታወስ፤ የሲዳማ፤ የደቡብ ምዕራብ፣ የማዕከላዊ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ተቋቁመዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ለጠቅላላ ጉባኤው ከተሰጡ ኃላፊነቶች መካከል አዲስ አባልነቶችን ማፅደቅ አንዱ መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ በዚህም የጉባኤው የመጀመሪያ አጀንዳ ምክር ቤቶቹ የሚያቀርቡትን ጥያቄ በመቀበል የጠቅላላ ጉባኤው ተሳታፊ ማድረግ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት ምክር ቤቱ 18 አባላት እንደ ነበሩት የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ በቀጣይ የአዳዲስ ክልሎች አባልነት በጉባኤው ሲፀድቅ የአባላት ቁጥር ወደ 21 ከፍ የሚል ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢንጂነር መላኩ እንደተናገሩት፤ በወቅቱም የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት ይመረጣል። የምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ እጩዎችን የሚያቀርቡበት አሠራር አለ። በዚህ መሠረት እስከ ሰኔ 25 ሦስት ዕጩዎች ለፕሬዚዳንትነት እና አምስት ዕጩዎች ለምክትል ፕሬዚዳንትነት ቀርበዋል።

10ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በተለያዩ ምክንያቶች ለአራት ዓመት ሊዘገይ ችሏል። ጉባኤው የሚካሄደው የክልል እና የከተማ ምክር ቤቶች ጉባኤያቸውን ካደረጉ በኋላ ሲሆን፤ በ2012 ዓ.ም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላላ ጉባኤውን ባለማድረጉ ሊዘገይ ችሏል።

በሌላ በኩል በሰሜኑ ጦርነት፤ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለሁለት በመከፈሉ ጉባኤው እንዲራዘም የተደረገ ሲሆን እንዲዘገይ የተደረገው እግድ ከተነሳም በኋላ አንዳንድ ክልሎች በጉባኤው እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን መስፈርት ባለሟሟላታቸው በተጨማሪ ሊዘገይ እንደቻለ ገልፀዋል።

አባል ምክር ቤቶች በጠቅላላ ጉባኤው እንዲሳተፉ፤ አምስት መስፈርቶች መኖራቸውን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ፣ የራሳቸውን ጠቅላላ ጉባኤ ማድረግ፣ የአባልነት መዋጮ ማዋጣት፣ የአባላት መረጃ ማቅረብ እና የምስክር ወረቀት ማሟላት እንደሆነ ተናግረዋል።

በመጨረሻም አባላቱ መስፈርቱን ባያሟሉም ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ያሉዋቸው ምክር ቤቶች በጉባኤው ተሳትፈው፤ ጉባኤው እንዲካሄድና ያልተሟላው መስፈርት ቀጣይ በሚመረጡ የቦርድ አባላት እንዲታይ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በመወሰኑ፤ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም በአፍሪካ ኅብረት አዳራሽ ይካሄዳል ብለዋል።

የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ ውቤ መንግሥቱ በበኩላቸው፤ በጉባኤው ለመሳተፍ የሚያስችሉ መስፈርቶች አለመሟላት በሀገር አቀፍ ምክር ቤቱ ላይ ክፍተት ይፈጥራል ሲሉ ገልጸዋል።

መስፈርቶች መሟላት አለባቸው ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ ያ ሲሆን የተሻለ አደረጃጀት እና የንግድ አካባቢ ይፈጠራል። መስፈርቶች አለመሟላታቸው በምክር ቤቱ አሠራር ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል ብለዋል።

መስፈርቶቹ እንዲሟሉ በአዋጅ የተቀመጠ ቢሆንም፤ መንግሥት እራሱ እየገባ መስፈርቶችን የመተው ነገር አለ። በየደረጃው ያሉ አባላት የተሻለ አቋም እንዲኖራቸው ሚዲያው የራሱን ድርሻ እንዲወጣ ጥያቄ አቅርበዋል።

# ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል ከነገ ጀምሮ ይካሄዳል

**ሞገስ ፀጋዬ**




አዲስ አበባ፡- ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል በአዲስ አበባ ለ9ኛ ጊዜ ከነገ ጀምሮ ሊካሄድ መሆኑን የአዲስ አበባ ባሕል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ባሕልና ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ ‹‹ንባብ ለትውልድ ግንባታ›› በሚል መሪ ሃሳብ ለ9ኛ ጊዜ ከተማ አቀፍ የንባብ ባሕል ፌስቲቫል ከሰኔ 28 እስከ 30 ቀን 2016 ዓ.ም በኤግዚቢሽን ማዕከል ሊያካሂድ ነው።

ፌስቲቫሉን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጡት በአዲስ አበባ ከተማ ባሕልና ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ የባሕል ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አስፋው ኩማ እንደገለጹት፤ የኤግዚቢሽኑ ዋና ዓላማ ወጣቱ አንባቢ ተመራማሪና በአመክንዩ ላይ የተመሠረተ ችግር ፈቺ ሀሳብ እንዲያፈልቅ ማድረግ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ባሕልና ኪነጥበብ ቱሪዝም ቢሮ የንባብ ባሕልን ለማዳበር በየዓመቱ የንባብ ፌስቲቫል ያካሂዳል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ አንባቢ ትውልድ እንዲፈጠር የንባብ ንቅናቄ ያስፈልጋል። ተማሪዎች ትምህርት የጨረሱበት ጊዜ በመሆኑና ሕጻናት ከማንበብ ይልቅ ማኅበራዊ ሚዲያን በስፋት ሲጠቀሙ የሚስተዋልበት በመሆኑ ይህን ለመቀየርና የንባብ አስፈላጊነትን ለማሳየት የንባብ ፌስቲቫል መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ማብራሪያ፤ በፌስቲቫሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በሥነ-ጽሑፍ፣ በስፔሊንግ-ቢ እና በጠቅላላ ዕውቀት ውድድር የሚካሄድ ሲሆን ለመጽሐፍት አሳታሚዎችና መጽሐፍት ሻጮች የገበያ ዕድል እንደሚፈጠር ገልጸዋል።

የፌስቲቫሉ መካሄድ ተማሪዎች የክረምት ጊዜያቸውን በንባብ እንዲያሳልፉና የንባብ ባሕላቸውን እንዲያዳብሩ፣ ወላጆች ልጆቻቸው የንባብ ጊዜ እንዲኖራቸው ትኩረት እንዲሰጡ እንደሚያስችል ጠቁመው፤ በከተማዋ የሚገኙ የሕዝብ ቤተ መጽሐፍት ያሉበትን ደረጃ ለነዋሪዎች ለማስተዋወቅ ያግዛል ብለዋል።


እንደ አቶ አስፋው ገለጻ፤ በፌስቲቫሉ ልጆች እውቀት እየቀሰሙ የሚጫወቱበት ሲሆን የሰርከስ ትርዒት፣ ብስክሌት መንዳትና የተለያዩ የልጆች የመዝናኛ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል።

የከተማዋ ነዋሪዎች በፌስቲቫሉ ላይ ከልጆቻቸው ጋር በመታደም ንባብን ባሕል ያደረገ ትውልድ ለመፍጠር በሚደረግ ሂደት ውስጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀርቧል።

ፌስቲቫል ላይ የመንግሥትና የግል ቤተ መጽሐፍት፣ ደራሲያን፣ የመጽሐፍት አሳታሚዎች፣ በመጽሐፍት ሽያጭ ላይ የተሰማሩ አካላት፣ የግል ትምህርት ቤቶች፣ መንፈሳዊ ኮሌጆች ቤተ መጽሐፍት እንደሚገኙ ተገልጿል።

# ኢፕድ ተልዕኮውን ከመወጣት ጎን ለጎን ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በትጋት እየተሳተፈ ይገኛል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ ከመወጣት ጎን ለጎን ሀገራዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በትጋት እየተሳተፈ ይገኛል ሲሉ የድርጅቱ የይዘት ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አመራሮችና ሠራተኞች በእንጦጦ ፓርክ በመገኘት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ትናንት አካሂደዋል፡፡ የዘንድሮ አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር “የሚተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ” በሚል መሪ ሃሳብ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ከተማ በዕለቱ እንደገለጹት ድርጅቱ ተልዕኮውን ከመወጣት ጎን ለጎን ሀገራዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በትጋት እየተሳተፈ ይገኛል፡፡

የአረንጓዴ ዐሻራ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከተጣለበት ሀገራዊ ኃላፊነት ወጪ እንደ ትልቅ ተልዕኮ ይዞ ከሚሠራባቸው አጀንዳዎች ውስጥ ቀዳሚ ነው ያሉት ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የአረንጓዴ ዐሻራ እንደሀገር ከተጀመረ አንስቶ እንደ ተቋም ዘገባ በመሥራት ኃላፊነቱን እየተወጣ እያንዳንዱ ሠራተኛና አመራር ደግሞ እንደ ዜጋ ዐሻራውን እያሳረፈ ይገኛል ብለዋል፡፡

አረንጓዴ ዐሻራ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ባሕል እንዲያደርገው በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ የማስተማርና የማስተዋወቅ ሥራ በትኩረት ሲሠራ መቆየቱንም ሲሉ ነው አቶ ፍቃዱ ያብራሩት፡፡

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለጻ፤ ድርጅቱ በደም ልገሳ፣ የተለያዩ ድጋፍና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም ሠራተኛው በወርሐዊ ደመወዙ ለመቄዶኒያ ድጋፍ እንዲያደርግ በማድረግ ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ እየተሳተፈ ይገኛል፡፡

አረንጓዴ ዐሻራ የአየር ንብረት ለውጥ መቀነስና በየዘርፉ ላይ ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሀገሪቱ የደን ሽፋን ከነበረበት ሦስት በመቶ ወደ ከ27 በመቶ በላይ መድረሱ ተስፋ ሰጪ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የአረንጓዴ ዐሻራ የአየር ንብረት ለውጥ ከመቀነሱም በላይ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ፣ የሥራና የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ውጤት እያስገኘ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የኮርፖሬት ዘርፍ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድም ተክሉ በበኩላቸው ድርጅቱ የአረንጓዴ ዐሻራ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በቂሊንጦና በእንጦጦ ፓርኮች ላይ የተለያዩ ችግኞች በመትከል በንቃት ሲሳተፍ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

የተተከሉ ችግኞች ከመንከባብ አኳያ ሥራዎች ቢሠሩም አሁንም ተጨማሪ ሥራዎች መሥራት ይጠይቃል ያሉት አቶ ወንድም፤ በቀጣይ የተተከሉ ችግኞችን መንከባከብ እንዲቻል ሠራተኛው በራሱ ተነሳሽነት መዋጮ አዋጥቶ እንክብካቤ ለሚያደርግ አካል እንዲሰጥ እንዲሁም በዓመት ሦስት ጊዜ በቦታው በመገኘት ክትትል እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባለፉት ዓመታት የተከላቸው ችግኞች 80 በመቶ ፀድቀዋል ያሉት ደግሞ የእንጦጦ ፓርክ የችግኝ ባለሙያ አቶ አስቻለ ደሳለኝ ናቸው፡፡

አቶ አስቻለ አክለውም፤ ድርጅቱ ያለማቋረጥ በፓርኩ ውስጥ ችግኝ እየተከለ እንዲሁም እየተከታተለ ይገኛል ያሉ ሲሆን ሌሎች ተቋማትም ከዚህ ልምድ በመውሰድ አንድ የራሳቸው ቦታ ወስደው ዐሻራቸውን ማኖር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡



# ሀገራዊ መረጃዎች እንዳይጠፉ ተቋማት ለሰነድ አያያዝና አወጋገድ ትኩረት እንዲሰጡ ተጠየቀ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ መረጃዎችን የያዙ ሰነዶች በእርጅና ምክንያት እንዳይጠፉ ተቋማት ለሰነድ አያያዝና አወጋገድ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ጠየቀ፡፡

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ዋና ዳሬክተር አቶ ይኩኑአምላክ መዝገቡ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የተለያዩ ተቋማት ለሥራ የሚያመነጯቸው ሰነዶች ከጊዜ በኋላ ሀገራዊ መዛግብት በመሆናቸው ተቋማት ለሰነድ አያያዝና አወጋገድ ልዩ ትኩረት ሊሠጡ ይገባል፡፡

እንደ አቶ ይኩኑአምላክ ገለጻ፤ በርካታ ተቋማት የቦታ ጥበት አጋጥሞናል በሚል ምክንያት መዛግብቶችን በጆንያ እያከማቹና ከሕግ አግባብ ውጪ ጥቅም አይሰጥም በሚል እስከማቃጠል የደረሱ አሉ፡፡

የሰነዶችን አያያዝ በሚመለከት የወጡ ጥብቅ ሕጎች ቢኖሩም ከግንዛቤ ማነስና በሌሎች ምክንያቶች አስፈላጊ ሰነዶች እየጠፉ ናቸው ብለዋል፡፡

ተቋማት የሥራ አካባቢያቸውን ማስዋባቸው ጥሩ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በማስዋብ ሂደት ውስጥ ለመረጃ ሀብቶች ልዩ ጥንቃቄ ማድረግና በአግባቡ መጠበቅ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ሰነዶች የምርምር ሥራዎችን ለመሥራት ትልቅ ጥቅም እንዳላቸው ጠቅሰው ከተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የመጡ ሰነዶችን በአግባቡ የማደራጀት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ተቋማት ሰነድ አያያዝን በዘመናዊ መንገድ መሰነድ እንደሚገባቸው ገልጸው አገልግሎቱ ያገለገሉ ሰነዶች ከሥርዓት ውጪ እንዳይወገዱ ክትትል እያደረገ መሆኑን አቶ ይኩኑአምላክ አስረድተዋል።

በርካታ ሰነዶች እለታዊ ፋይዳ ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሰው ከነዚህ ውስጥ ወቅትን፣ ባሕልንና ትውፊትን የሚገልጹ አመላካች ሰነዶች ወደ መዛግብትነት ተቀይረው እንዲጠበቁ ይደረጋል ብለዋል፡፡

አገልግሎቱ ከእንቅስቃሴ ውጪ የሆኑ ሰነዶችን በሕጋዊ መንገድ ለማስወገድ የሚያስችል ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እንደሚሠራ አስረድ ተዋል፡፡

በቀጣይ ስለሰነዶች አወጋገድ ግንዛቤ የማስጨበጥ፤ ሕጉን በተጠናከረ መልኩ የማስፈጸም፣ የመረጃ ሀብቶች በአግባብ እንዲጠበቁ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ስለመዛግብትና ሰነዶች አወጋገድ የሕግ ማዕቀፍ ጥናት ያቀረቡት የሕግና የታሪክ ተመራማሪው አልማው ክፍሌ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሰነዶችን ለማስወገድም ሆነ ለመጠበቅ ባሉበት ተቋም እስከ 25 ዓመት መቆየት ይኖርባቸዋል፤ ከዚያ በኋላ ግን ወደ አገልግሎቱ እንዲመጡ ተደርጎ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የማስወገድና የመጠበቅ ሥራ ይሠራል፡፡

እንደ ሀገር መዝገብ ቤት ለሚመደብ ባለሙያ የተሳሳተ ግምት የመስጠት ልማድ መኖሩ ለሰነዶች መበላሸትና መጥፋት ምክንያት ሆኗል ያሉት አልማው (ዶ/ር) ለመሰል ድርጊቶች ተቋማት በተገቢው ትኩረት ካልሰጡ ትልቅ ጉዳት እንደሚያስከትል ተናግረዋል፡፡

# የቡና አምራች፣ አቅራቢና ላኪን እያገናኘ ያለው የቀጥታ የግብይት ሥርዓት የውጪ ንግድ ገቢን እያሳደገ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

ጅማ፡- በቡና አምራች፣ አቅራቢና ላኪ መካከል የተፈጠረው የቀጥታ የገበያ ትስስር ከውጪ የቡና ንግድ የሚገኘውን ገቢ እያሳደገ ነው ሲል የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ።

ሀገራዊ የቡናና ቅመማ ቅመም ኤግዚቢሽን በጅማ ከተማ እየተካሄደ ነው።

ኤግዚቢሽኑ በቡና፣ በቅመማ ቅመም ዘርፍ ላይ ለተሠማሩ አምራቾች፣ አቅራቢዎችና በላኪዎች መካከል የተዘረጋውን የቀጥታ የግብይት ሥርዓት በማጠናከር ተጠቃሚነታቸውን ለማስፋትና ሀገሪቱ የምታገኘውን የውጪ ገቢ ለማሳደግ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ተብሏል።

የኤግዚቢሽኑን መከፈት አስመልክተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር)፤ በቡና አምራች፣ በአቅራቢና በላኪ መካከል የተፈጠረው ቀጥታ የገበያ ትስስር ሀገሪቱ ከቡና የውጪ ንግድ እያገኘች ያለውን ገቢ በማሳደግ ትልቅ ለውጥ እያስገኘ ነው።

በቡና አምራች፣ አቅራቢና ላኪ መካከል የተፈጠረው ቀጥታ የገበያ ትስስር ሀገሪቱ የምታገኘውን የቡና የውጪ ገቢ ከማሳደግ ባለፈ በዘርፉ የተሠማሩ አምራቾች፣ አቅራቢዎችና ላኪዎችን የገቢ አቅም እያሳደገ ነው ብለዋል።

የቡናን ምርት በጥራት አምርቶ ለውጪ ገበያ በማቅረብ የሀገሪቱ የውጪ ገቢ እያደገ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሀገሪቱ ከቡና የወጪ ንግድ የምታገኘው ገቢ ከሚሊዮን ዶላር ወደ ቢሊዮን ዶላር ማሳደግ ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

ቡናን በጥራት አምርቶ ለውጭ ገበያ በማቅረብ እየተገኘ ያለው ገቢ እያደገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በ2014 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር፣ በ2015 በጀት ዓመት አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን አብራርተዋል፡፡ በተያዘው ዓመት ከፍተኛ የውጪ ዶላር ተገኝቷል ብለዋል።

እንደ አዱኛ (ዶ/ር) ገለጻ፤ በአምራቾች፣ በአቅራቢዎችና በላኪዎች መካከል የቀጥታ የግብይት ሥርዓት ባልነበረበት ወቅት አቅራቢና ላኪ በአካል አይተዋወቁም ነበር። ሁለቱም በወኪሎቻቸው ነበረ የሚገናኙት፡፡ ወኪሎቻቸው በቆረጡላቸው ዋጋ እንዲገበያዩ ይገደዳሉ፤ ይህም አቅራቢዎች ከላኪዎች የተቆረጠው ገንዘብ እንዳይደርሳቸው አድርጎ ቆይቷል።

አሁን የተጀመረው በዘርፉ የተሠማሩትን አካላት በቀጥታ የገበያ ትስስር የማገበያየት ሥራ ደላላዎችን ከመካከል በማውጣት ችግሩ እየተፈታ ነው ብለዋል።

ደላላው ከገበያ ሥርዓቱ እንዲወጣ መደረጉ አምራች፣ አቅራቢና ላኪውን በገቢ እያሳደገ ነው። ሀገሪቱም በቡና የውጪ ንግድ ገቢ አቅሟ እያደገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በዘርፉ እየተሠራ ያለው አምራችን፣ አቅራቢንና ላኪን በቀጥታ የማገናኘት ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ወይዘሮ መሠረት አሰፋ በበኩላቸው፤ የአምራች፣ የአቅራቢና የላኪዎች ቀጥታ የገበያ ትስስር የሀገሪቱን የውጪ የቡና ንግድ ገቢ እያሳደገ መሆኑን ተናግረዋል።

አምራቾችን፣ ከአቅራቢዎች፣ አቅራቢዎችን ከላኪዎች ጋር በቀጥታ ተገናኝተው ግብይት እንዲያደርጉ መደረጉ በገበያ ሥርዓቱ የነበረውን ችግር እየፈታ ነው ብለዋል።

የቀጥታ የንግድ ትስስር በገበያ ደላላዎች ከመሐል እንዲወጡ ስላደረገ በአምራች፣ በአቅራቢና በላኪ መካከል ያለው ችግር እየተፈታ መሆኑን ጠቁመው፤ የቀጥታ ገበያ ትሰስር የመፍጠሩ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

# በኢትዮጵያ አንድ ተሽከርካሪ በአማካኝ ከመቶ በላይ ዜጎችን እያገለገለ ነው

## -ኢትዮ አውቶሞቲቭ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኤክስፖ ትላንት ተከፍቷል

ማርቆስ በላይ



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተሽከርካሪ ቁጥር ከሰው ስብጥር አንጻር አንድ ተሽከርካሪ በአማካኝ ከመቶ በላይ ዜጎችን እያገለገለ መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ከኢትዮ አውቶቴክ ትሬዲንግ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ኢትዮ አውቶሞቲቭ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ኤክስፖ ትላንት በሚሊኒየም አዳራሽ ተከፍቷል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የተሽከርካሪ ቁጥር ከሰው ስብጥር አንጻር አንድ ተሽከርካሪ በአማካኝ ከመቶ በላይ ዜጎችን መሆኑን ጠቁመው፤ በአንጻሩ ኢትዮጵያ በጥቂት ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ ከሚያስመዘግቡ ሀገራት አንዷ ናት ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ረዥም ጊዜ ያገለገሉ መሆናቸው፣ የተሽከርካሪ ጥገና፣ ምርመራና ቁጥጥር፣ አወጋገድ ሥርዓት በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸው ለሀገሪቱ ለከፍተኛ የሰው ሞት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት መዳረጉን አስረድተዋል፡፡

የትራፊክ አደጋ በአሽከርካሪዎች ብቃትና ሥነ ምግባር፣ በተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ችግር ሳቢያ የሚከሰት መሆኑን በመግለጽ፣ የትራፊክ አደጋ አምራች የሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል በእጅጉ እያሳጣ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የትራንስፖርት ዘርፉ የሚመራበት ፖሊሲ፣ የሎጂስቲክስ፣ የ30 ዓመት ማስተር ፕላን፣ የተሽከርካሪዎች እስታንዳርድ፣ የካርበን ልቀት ስታንዳርድ እንዲዘጋጁ በማድረግ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የሕዝብን ተጠቃሚነት በተጨባጭ ያረጋገጡ ውጤቶች መመዝገባቸውን በመግለጽ፣ በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ ያሉት የተሽከርካሪዎች ብዛት ካለው የሕዝብ ብዛት አንጻር ዝቅተኛ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሀገሪቱ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ባስመዘገበችው የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ፍላጎት በየጊዜው እየጨመረ መቷል ያሉት ሚኒስትሩ በሀገሪቱ ፈጣንና ቀጣይነት ባለው የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪው በሚፈለገው ደረጃ ባለመደራጀቱ ከዘርፉ የሚገኘው ጥቅም አልተገኘም ብለዋል፡፡

የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪው ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች አንዱ በመሆን በሀገሪቱ ብሔራዊ ልማት ውስጥ ቁልፍ ሚና መጫወቱን ጠቅሰው፣ ዘርፉ ለአጠቃላይ ሀገራዊ እድገት መሠረት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኤክስፖው ላይ የተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት፣ የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ኩባንያዎችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚሳተፉበት ሲሆን ከሰኔ 26 እስከ 28 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ ይሆናል።

## ንቅናቄው ሕገወጥነትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ተገዥነት ንቅናቄ ማጠቃለያና የቀጣይ ዓመት ማስጀመሪያ መርሐ ግብር በዛሬው ዕለት ይካሄዳል፡፡

በንቅናቄው የተከናወኑ ተግባራትንና የቀጣዩን ዓመት ማስጀመሪያ መርሐግብርን አስመልክቶ መግለጫ የሰጡት የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሤ እንደገለጹት፤ ለአንድ ዓመት ሲካሄድ በቆየው መርሐግብር በታክስና የጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ላይ በተከናወኑ ሥራዎች ሕገወጥነትን በመከላከል ገቢ የመሰብሰብ አቅምን ማሳደግ ተችሏል፡፡

በንቅናቄ መርሐግብሩ ግብር ከፋዮችን ማበረታታትና ከታክስ ሥርዓት የራቁ የኅብረተሰቡ ክፍሎችን ወደ ታክስ ሥርዓት እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

ከአራት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ግብር ከፋዮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ እውቅናና ሽልማት መበርከቱን ገልጸው፤ የንቅናቄው ማጠቃለያና የቀጣይ ዓመት ማስጀመሪያ መርሐግብር በዛሬው ዕለት የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት እንደሚከናወን ገልጸዋል።

ንቅናቄው ግብርን በወቅቱ የሚከፍሉና ለታክስ ሕጉ ተገዢ የሆኑትን ማብዛት ዓላማ ያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ግብር የሚሰውሩ አካላት ወደ ሕግ ተገዢነት ለማስገባት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የሕግ ተጠያቂነት ማረጋገጥ፣ አሠራሮችን የማዘመን ሥራዎች እንዲሁም በሁለት ከተማ አስተዳደሮችና ስምንት ክልሎች በሚገኙ 240 ትምህርት ቤቶችና ክበባት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች መሠራታቸውን ሚኒስትሯ ጠቁመዋል።

በግብር ከፋዮችና በኅብረተሰቡ በኩል ጠንካራ የታክስ እውቀት እንዲኖር እና ሕገወጥነትን የሚጠየፍ ዜጋ ለመፍጠር አስቻይ ሁኔታዎች መኖራቸውን አንስተዋል፡፡

የታክስ ገቢው ከጠቅላላ ሀገራዊ ገቢ አንጻር ብዙ መሥራት ይጠይቃል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ለዚህም የታክስ አሰባሰብ ሄደቱን ለማዘመን የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በቴሌ ብር አማካኝነት መክፈል በመቻላቸው በገቢ አሰባሰቡ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ንቅናቄው ለተቋም ግንባታ አስተዋፅዖ ማድረጉን አውስተው፤ ግብር የመክፈል ባሕልን ለማሳደግ የሚረዱ ሥራዎችን ለመሥራት መታቀዱን ገልጸዋል።

ኮንትሮባንድን ለመከላከል እንዲሁም ለመቆጣጠር ከፌዴራልና ከክልል የፀጥታ አካላት ጋር ጠንካራ ሥራ መሥራት በመቻሉ ጥሩ ውጤቶች መገኘታቸውን አስረድተዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የታለመውን የልማት እቅድ ለማሳካት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የገቢ አሰባሰብ ማሻሻልና በሕጋዊ መንገድ እንዲመራ የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸው አመላክተዋል፡፡

## ኢትዮጵያውያን የተረጂነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በተለያዩ ጊዜያት የሚከሰቱ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ተረጂነትን እንድንለማመድ አድርጎናል ያሉት አቶ አሕመድ በአንድነትና በመተባበር ያሉንን ሀብቶቻችን መጠቀም እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

እንደ ሀገር ያሉ ዕድሎችን በመጠቀም ከጠባቂነት ወደ እራስን መቻል መሸጋገር እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል፡፡

ለተረጂነት ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮችን በራስ አቅም ምላሽ መስጠት የሚያስችል ሀገራዊ አቅም አለመፈጠሩ ለተረጂነት ሥነ-ልቦና ልምምድ አስተዋፅዖ ማድረጉን አመላክተዋል፡፡

ተረጂነት አንገት የሚያስደፋ በመሆኑ ወደ ምርታማነት ለመሸጋገር ያሉትን ሀብቶች በአግባቡ መጠቀም ይገባናል ያሉት አቶ አሕመድ፤ መንግሥት የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረግ አለበት ብለዋል፡፡

ለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተረጂነት ባሕልን ለመቅረፍ የሚያስችል የንቅናቄ ሥራ መሠራት እንዳለበት አውስተው እንደ ስንዴ ልማት ያሉ ሥራዎችን በተጠናከረ መልኩ ማስቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

እንደ አደጉ ሀገራት ሕጻናትን ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እራሳቸውን እንዲችሉና ጠባቂ እንዳይሆኑ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ አካቶ የማስተማር ሥራ መሠራት አለበት ብለዋል፡፡

ኅብረተሰቡ የተረጂነት እሳቤን በመስበር ለተሟላ የኢኮኖሚ ነፃነት በቁጭት በመነሳትና ከዚህ ለመላቀቅ ከውጪ የመጠበቅ የመሰሉ አስተሳሰብን ከምንጩ ማድረቅ ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ሠላምና ልማት የማይነጣጠሉ ጉዳዮች በመሆናቸው ተረጂነትን ለማሸነፍ ሀገራዊ ሠላምን ማስጠበቅ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

የሀዳ ሲንቄዎች ጉባኤ አባል ሀዳ ሲንቄ ሳራ ዱቤ በበኩላቸው፤ ክብረ ነክ የሆነውን ተረጂነት ለማስወገድ የቁጠባና የመደጋገፍ ባሕልን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ተረጂነትን ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት እንደሚቻል ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም የልማት ሥራዎች የተመዘገቡ ውጤቶች ማሳያ እንደሆኑም አንስተዋል።

መንግሥት በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በሌማት ትሩፋትና በኢንዱስትሪ ዘርፎች እየሠራ ያለው ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል እንዳለበት ገልጸው ከተረጂነት ለመላቀቅና ምርታማነትን ለማሳደግ ሁሉም ዜጋ ሚናውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል፡፡

## የአየር ንብረት ለውጥ እያደረሰ ያለውን ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ እቅዶቹ በአግባቡ እንዲፈጸሙ ኅብረተሰቡና አጋር አካላት እንዲተባበሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከአምስት ዓመታት በፊት በአራት ዓመታት 20 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ የተጀመረው መርሐ ግብሩ፤ እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ ከ32 ቢሊዮን በላይ ችግኞች መትከል የተቻለበት መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የነበሩ 45 ሺህ የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎችን ቁጥር ወደ 121 ሺ ከፍ ማለቱንና በማኅበረሰቡ ባሕል መሆን እንደቻለም አመልክተዋል፡፡

ከአየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆነው የስንዴ ልማት መርሐ ግብር በአየር ንብረት ለውጥ እየደረሰብን ያለውን ተፅዕኖ ለመቋቋምና መሰል ችግሮች ሲከሰቱ ምላሽ ለመስጠት አቅም የፈጠረ መሆኑን፣ በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረግ ሂደት አይነተኛ መርሐ ግብር መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

የታዳሽ ኢነርጂ አቅርቦት መርሐ ግብር ሥራ ኢትዮጵያውያንን ከጨለማ ወደብርሃን፣ ከማገዶ እንጨት ወደ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት በፍትሐዊነት ያሸጋገረ መሆኑንም ነው የጠቀሱት፡፡

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ድርቅና ጎርፍ መከሰታቸውን፣ ችግሮቹን ተከትለውም ተያያዥ የጤና፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፈጠራቸውንም ተናግረዋል፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የትግበራ መርሐ ግብሩ የወደፊቷን ኢትዮጵያ መልክ በመቅረጽ ረገድ የራሱ ድርሻ ያለው፣ ለኢትዮጵያን ብሎም ለአፍሪካን መልካም አጋጣሚ የሚፈጥር፣ ከተረጂነትም የሚያላቅቅ አቅጣጫ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

እአአ ከ1980 ጀምሮ ቢያንስ 10 ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱ ድርቆች መከሰታቸውን፣ ኢትዮጵያን ባልተገባ ስም ማስጠራታቸውን፣ በርካታ ጎርፎች ተከስተው ንብረትና መሠረተ ልማት ማውደማቸውን አስታውሰዋል።

እ.አ.አ ከ1999 እስከ 2008 የአየር ንብረት ለውጥ ባይኖር እንደርስበት ይገባ ከነበረው ጥቅል የኢኮኖሚ እድገት ስድስት ነጥብ አንድ በመቶ መቀነሱን አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱም ጠቁመዋል።

ችግሩን መቀልበስና ተገቢ ምላሽ መስጠት የሚቻለው በቁርጠኝነትና በትብብር መሥራት ሲቻል መሆኑን ጠቁመዋል። ለዓለም የገባነውን ቃል እውን ለማድረግ ከልማት አጋር አካላት ጋር መደጋገፍና መተባበር አለብን ብለዋል፡፡

ከአፍሪካዊ ወንድሞቻችን ጋር በትብብር ለመሥራት ዝግጁ ነን፤ በአረንጓዴ ዐሻራና በታዳሽ ኃይል ኢነርጂ ቀጣናዊ ትስስር በማድረግ ትብብር እያደረግን እንገኛለን ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በፓሪሱ ስምምነት የተቀመጠውን የአንድ ነጥብ አምስት ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ግብ ማሳካት የሚችሉ ተብለው እውቅና ከተሰጣቸው ሀገራት ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗንም አስታውሰዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ የባሕር በር የማግኘት መብቷ ሊረጋገጥላት ይገባል !

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በቀይ ባሕር ላይ ይዞታ የነበራትና ቀይ ባሕርንም ስታዝበት የኖረች ሀገር ነች:: 1 ሺህ 800 ኪሎሜትር የሚረዝመውን የቀይ ባሕር ይዞታ የነበራትና ለወጭና ገቢ እቃዎች ሁለት ወደቦች የምታስተዳድር ሀገር ነበረች:: ኢትዮጵያን ከቀይ ባሕር ውጪ ቀይ ባሕርንም ከኢትዮጵያ ውጭ ማሰብ ከባድ ነው::

ሆኖም የኢትዮጵያን ማደግ በማይፈልጉ ኃይላት ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር እንድትወገድ ተደርጓል:: ለዘመናትም ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ምንም ድርሻ እንዳልነበራት ሆን ተብሎ በተሰራጨው ትርክት እና በተሠራው ሴራ ኢትዮጵያና ቀይ ባሕር ተቆራርጠው ኖረዋል:: ከ60 ኪሎ ሜትር የባሕር ርቀት ላይ እየተገኙ ኢትዮጵያውያን ወደብ እና የባሕር በር እንዳይኖራቸው ተፈርዶባቸው ቆይተዋል::

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከሥነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል::

ለበርካታ መሠረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል:: በዲፕሎማሲ እና በተፅዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የባሕር በር አለመኖር የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው::

በኢትዮጵያ አዲስ የመንግሥት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሠራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባሕር በር ጥያቄ ነው:: መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባሕር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል:: የባሕር በር ማጣት ስብራትን በማከም አዲስ ታሪክ ለመጻፍ የባሕር በር የምታገኝበት አማራጮችን በማፈላለግ ላይ ይገኛል ::

ሠላማዊ አማራጭን ሲከተል የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ከሶማሊ ላንድ ጋር የባሕር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) በመፈራረም ተዘግቶ የነበረውን የኢትዮጵያውያንን የባሕር በር ጥያቄ ዳግም ወደ መድረክ አምጥቶታል:: በዚህ ኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ደስታ ስሜት ተሰምቷቸዋል::

መንግሥት የጀመራቸው ጥረቶች አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ በር የሚከፍት ነው:: ቀጣናዊ ሠላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆንም በር ይከፍታል::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት 16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ 126 ሚሊዮን ደርሷል:: በአጠቃላይም በኢትዮጵያ የሚኖረው ሕዝብ የባሕር በር ከሌላቸው ሁሉም ሀገራት ሕዝብ 1/3ኛውን ይሸፍናል::

ይሄንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ የባሕር በርና ወደብ የተነፈገ ሀገር የለም:: ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ በባሕር በር የተከበበች ሀገር ናት:: በሴራ እና በተሳሳተ ትርክት ከቀይ ባሕር እንድትርቅ ከመደረጓ በስተቀር አፈጣጠሯ ከቀይ ባሕር የሚነጠል ሊሆን አይችልም:: በሌላም በኩል በታሪክ ረገድም በቀይ ባሕር ላይ ለዘመናት የበላይ ሆና መቆየቷን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ያሏት ሀገር ናት::

ስለዚህም ኢትዮጵያ በሴራ ከባሕር በር ይዞታዋ እንድትነቀል ከመደረጓ ውጪ ባለቤትነቷን የሚከለክላት አንዳችም ዓለም አቀፍ ሕግ የለም:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባሕር የተደረገበት አካሄድ ምንም አይነት ሕጋዊ መሠረት የሌለው ነውና::

ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር እንድትወገድና ወደብ አልባ እንድትሆን የተደረገው በ1900፣ 1902 እና 1908 ከቅኝ ገዢዎች በተደረጉ ውሎች አማካኝነት ነው:: እነዚህ ውሎች ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት መመሥረቻ ቻርተር ሕጋዊነታቸውን አጥተዋል::

ስለዚህም ኢትዮጵያን የወደብ ባለቤት እንዳትሆን የሚያግዳት አንዳችም ማስረጃ የለም:: በመሆኑም አማራጭ የወደብና የባሕር በር ማግኘት ለኢትዮጵያውን የሕልውና ጉዳይ መሆኑን መገንዘብና ለዚህም የተለያዩ የሠላም አማራጮችን በመጠቀም የሀገሪቱን እና የሕዝቧን ዘላቂ ጥቅም ማረጋገጥ የግድ ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የተሻለ የፈተና ውጤት የሚመዘገበው፣ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓት ሲኖር ነው!

**ወንድይራድ ሰይፈሚካኤል**

የ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ብሔራዊ ፈተና ከትግራይ ክልል ውጭ ባሉ አካባቢዎች ከሐምሌ ሦስት እስከ ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲሁም በትግራይ ክልል ደግሞ ከሐምሌ ሁለት እስከ ሐምሌ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ እንደሚሰጥ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ይፋ አድርጓል:: የዘንድሮው ፈተና እንደቀድሞው በወረቀት ብቻ ሳይሆን በኦንላይንም እንደሚሰጥም ተገልጿል::

ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ በተለይም በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም፣ የተመዘገበው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግቢያ ፈተና ውጤት እጅግ አስደንጋጭ እንደነበር ይታወሳል:: የትምህርት ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው የፈተናው ውጤት መረጃ መሠረት፣ በ2014 ዓ.ም ፈተናውን ከወሰዱ 899ሺ 520 ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ ውጤት (ከ350 በላይ) ማስመዝገብ የቻሉት 29ሺ 909 (3.3%) እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ደግሞ 845 ሺህ ተማሪዎች ፈተናውን ወስደው ከግማሽ በላይ ውጤት ያመጡት ተማሪዎች 27 ሺ 267 (3.2%) ብቻ መሆናቸው ይታወሳል::

ውጤቱ ይፋ ከተደረገ በኋላ ብዙ ዓይነት አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ነበር:: ከአስተያየቶቹ መካከል አንዱ ከግማሽ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ የትምህርት ጥራት አለመኖሩን የሚያመለክት እንደሆነ የሚገልፀው ሃሳብ ነበር:: ለትምህርት ጥራት መጓደሉም መንስዔዎች ናቸው የተባሉ ብዙ ምክንያቶችም ተጠቅሰዋል:: የሆነው ሆኖ፣ የፈተናው ውጤት አስደንጋጭና አስገራሚ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም:: ከአጠቃላይ ተፈታኞች መካከል አራት በመቶ ያህሉ እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው ‹‹ሀገር ተረካቢ ነው›› ስለሚባለው ትውልድ በእጅጉ እንድንጨነቅ ያስገድደናል::

የፈተናው ውጤት በምን ዓይነት የትምህርት ሁኔታ ውስጥ እያለፍን እንደምንገኝ በግልፅ አሳይቷል:: አራት ከመቶ ተፈታኞች እንኳ ከግማሽ በላይ ውጤት አለማስመዝገባቸው ትምህርትን እንዴት እየቀለድንበት እንደሆነ ጥሩ ማሳያ ነው:: ይህ ደግሞ የሀገር ግንባታ ዋነኛ መሠረት የሆነው ዓምድና የሀገሪቱ ሕልውና እጅግ አስደንጋጭ አደጋ ውስጥ እንደገባ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው:: ታዲያ ይህ የሆነው በእርግማን ወይም በክፉ ምኞት ሳይሆን በትምህርት ጥራት ጉድለት ምክንያት ነው:: ጥራት በጎደለው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ተማሪ ጥሩ ውጤት ሊያስመዘግብ አይችልም::

የዘንድሮ ፈተና ምን ዓይነት ውጤት እንደሚመዘገብበት ወደፊት የምናየው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቢያንስ ካለፉት ሁለት ዓመታት የባሰ ውጤት እንዳይመዘገብ መስጋት ሞኝ ወይም ሟርተኛ አያስብልም:: ዘንድሮ የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ በመንግሥትና በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተከናወኑ ተግባራትን በሐቀኝነት መገምገም ይገባል::

ተፈታኞች ወደ ፈተና ማዕከላት ከሚገቡበት ቀን ጀምሮ የሚደረግላቸው ጥበቃና ድጋፍ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ግብዓት ነው:: የዘንድሮው ፈተና እንደቀድሞው በወረቀት ብቻ ሳይሆን በኦንላይንም ጭምር የሚሰጥ በመሆኑ፣ ተፈታኞች ከቴክኖሎጂው ጋር ያላቸው ትውውቅና ያዳበሩት ቅርበት ከፈተናው ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት አለው::

የኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለትምህርት ዘርፍ መሻሻልና የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት አዎንታዊ አስተዋፅዖዎችን እንዳበረከተ ባይካድም፣ ዓይነተ ብዙና ውስብስብ ችግሮችም አሉበት:: የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በንድፈ ሀሳብ እንጂ የተግባር ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም።

የምዘና ሥርዓቱም ለተግባራዊ እውቀት ትኩረት አልሰጠም። ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየተፈጠረ አይደለም። የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራው ጎልብቶ ኢኮኖሚውን በሚፈልገው መጠን ሲያግዝም አይስተዋልም። ከትምህርትና ሥልጠናው እውቀት፣ ክህሎትና የሥራ ፈጣሪነት አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ትውልዱ ዲግሪና ዲፕሎማ (ወረቀት) አምላኪ ሆኗል። ይህም የትምህርት ዘርፉን ጉዞ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎታል::

የአንድ ሀገር የትምህርት ሥርዓት መበላሸት የሀገሪቱ ሕልውና አደጋ ውስጥ እንደገባ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል:: ሠላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ መረጋጋት ያለባት፣ ምጣኔ ሀብቷ ያደገና ፖለቲካዋ የሰከነ ሀገር እውን ማድረግ

**የዘንድሮው ፈተና እንደቀድሞው በወረቀት ብቻ ሳይሆን በኦንላይንም ጭምር የሚሰጥ በመሆኑ፣ ተፈታኞች ከቴክኖሎጂው ጋር ያላቸው ትውውቅና ያዳበሩት ቅርበት ከፈተናው ውጤት ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት አለው**

የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት የተገነባ ትውልድ ማፍራት ሲቻል ነው::

ጥራት በሌለውና በወደቀ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ትውልድ ለሀገር ሕልውና ትልቅ አደጋ ይሆናል:: ለዚህም ነው ‹‹አንድን ሀገር ለማፍረስ ጦር ማዝመት ሳያስፈልግ፣ የሀገሪቱን የትምህርት ሥርዓት ማበላሸት በቂ ነው›› የሚባለውን ሃሳብ በተደጋጋሚ የምንሰማው::

በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ፣ ለሕግ ዘብ የቆሙ፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ ሆነው አጠቃላይ ሰብዕናቸው የተገነባ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት ነው።

አንዲት ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው:: የሰው ኃይል መገንቢያው ዋነኛው መሣሪያ ደግሞ ትምህርት ነው:: አስተማማኝና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ብቸኛው መንገድ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓትን መዘርጋት ነው:: ‹‹ዋናው ሽፋን/ብዛት ነው፤ የጥራቱ ጉዳይ ቀስ ብሎ ይታሰብበታል›› የተባለው አካሄድ ለኢትዮጵያ ምን እንዳተረፈላት አይተናል:: የትምህርት ሥርዓቱ ብልሽት ሀገሪቱን ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል፤ እያስከፈላትም ይገኛል::

የትምህርት ጥራትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ተማሪዎችን ያማከለ ዘመናዊና አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደት መከተል፤ የመምህራን ጥራትና ተነሳሽነት ማጎልበት፤ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን መከተል፤ ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ ጠንካራ የትምህርት ቤት አመራርን ማብቃት፤ ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፤ የማስተማሪያ ግብዓቶች ማሟላት እንዲሁም የተማሪዎች ሥነ ምግባርን ማሳደግ ይገባል።

የተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚገባ የመከታተል፤ የመምህራን በጥራት የማስተማር፤ የትምህርት አመራር ስትራቴጂካዊ አመራር የመስጠት እንዲሁም የወላጆች ልጆቻቸውን በንቃት የመከታተልና የመደገፍ ተግባራት በቅንጅት ሊከናወኑ ይገባል። በትምህርትና ሥልጠና በቂ የሰው ኃይል ለማፍራት ባለፉት ዓመታት የትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የተሠሩ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት መገምገምም ይገባል::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ በሥነ ምግባር፣ በመልካም እሴትና በብቃት የታነጸ ዜጋን ለማፍራት በሚያስችል መንገድ የተቀረፀ፣ የሀገሪቱን ዕድገትና አንድነት የሚያስቀጥል እንዲሁ ስራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ለሥራ ፈጣሪነትና ለሀገር በቀል እውቀቶች ተገቢውን ትኩረት የሰጠ መሆኑን በሚገባ መፈተሽና ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተሻለ የፈተና ውጤት የሚመዘገበው፣ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓት ሲኖር ነው!

የትምህርት ሥርዓቱን/የመማር ማስተማር ሥራ በተግባር ተኮር እውቀት በመደገፍ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ ለማፍራት መጣር ያስፈልጋል:: አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ይህን ጥረት እውን ለማድረግ ትልቅ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል:: ስለሆነም በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ሥራ ፈጣሪነትን ባሕሉ ያደረገ ትውልድ እንዲፈጠር የትምህርት ሥርዓቱን ትግበራ በከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት መምራት ይገባል!

# ወቅታዊ

# " በአሁኑ ወቅት በክልሉ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር የለም "


ፎቶ፦ በረሁን ታደሰ

አቶ አሰም የሱፍ
በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሠላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ፣ የፀጥታ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግርማ መንግሥቴ

እንደ ሌሎች ክልሎች ሁሉ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም ችግር ገጥሞት ነበር። እንደ ማንኛውም አካባቢ በዚህ አካባቢም ሠላም ርቆ፣ ጠብ ነግሶ ቆይቷል። እንደ አገራችን ሌላኛው ስፍራ ደም ፈሷል፤ ውድ የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት ጠፍቷል። በስሩ ሰባት ወረዳዎች ያሉት መተከል ዞን በፌደራል ማዘዣ ማዕከል ትዕዛዝ ሥር እንዲተዳደር እስከ መወሰን ድረስ የዘለቀ ችግር የተፈጠረበት ክልል እንደ ነበር የሚረሳ አይደለም።

በወቅቱ፣ በተለይም በ2012 ዓ•ም አካባቢ ወልቂጤ፣ ሐዋሳ፣ አሶሳ እና ሌሎችም ቦታዎች ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ዜጎች በሌሎች ዜጎች ላይ ሰንዝረዋል። በጉጂ እና ጌዲኦ ዞኖች፣ በቄለም ወለጋ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ኢትዮ-ሶማሌ እና ኦሮሚያ ክልል በርካታ ግጭቶች ተከስተዋል፤ ሰዎች ተፈናቅለዋል፤ ውድ ሕይወታቸውንም አጥተዋል። እነዚህም ግጭቶች በተመለከተ በርካታ ዜናዎችና መረጃዎች በስፋት ይተላለፉ ነበር፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መሀመድ ሀምደኒል፣ በቀን 05/2012 ዓ/ም ከቀኑ 5፡00 አካባቢ ከአሶሳ ወደ ካማሼ በመሄድ ላይ ያለ የግል መኪና ማንነታቸው ያልታወቁ የታጠቁ ኃይሎች ከካማሺ መገንጠያ፣ ማቃ ቢላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መኪናውን በማስቆም በከፈቱት ተኩስ የአንድ የፖሊስ አመራር ሕይወት ማለፉን አስመልክተው አስተላልፈውት በነበረው የውግዘት መልእክት "በአካባቢዉው የሚንቀሳቀሱ ፀረ ሰላም ኃይሎች ሕዝቡ በአሁኑ ሰዓት መረጋጋቱን በማየትና ሠላሙን ለማደፍረስ ታስቦና ሆን ተብሎ የተደረገ እንጂ ተግባሩ ከካማሺ ሕዝብ ጋር ምንም የሚያገናኘው" ነገር እንደ ሌለ፤ ተግባሩ የፀረሠላም ኃይሎች እንጂ ሕዝቡን እንደማይወክል የገለፁትን መለስ ብሎ በማስታወስ፤ እንዲሁም በክልሉ (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል) በመንቀሳቀስና ሕዝቡን በመረዳት የክልሉን ሕዝብ ሲረብሹትና ሰላሙን ሲነሱት የነበሩት ከጉያው የወጡ ኃይሎች መሆናቸውን ያለ ማመንታት መናገር ይቻላል።

በጉባና በዳንጉር ወረዳዎች ተከስቶ የነበረውን የፀጥታ ችግር፤ የማኅበረሰቡን አብሮ የመኖር እሴት ለመሸርሸርና እርስ በርሱ ለማጫረስ ወዘተረፈ የተሄደበትን ርቀት ሳስታወሰ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አመራርና ሕዝብ ምን ምን አይነት ችግሮችን ፈንቅሎ እዚህ እንደ ደረሰ መገንዘብ አያዳግትም።

ዛሬ እንደምናየው ከመሆኑ በፊት በቤኒሻንጉል ክልል ፀጥታ እንደ ሰማይ ርቆ፤ ሰላም እንደ ንፋስ ብን ብሎ ጠፍቶ ዜጎች ሳልጠበቁት ሁለንተናዊ ቀውስ ተዳርገው ነበር። ለልማት የታጨው በጀት ለሰላም ማስከበር፤ ለምርትና ምርታማነት የታሰበው ጊዜ የአካባቢ ሰላምና ፀጥታ፤ እንዲሁም ደህንነትን ማስከበር ላይ ይውል ዘንድ ግድ ብሎ ነበር። ይህ ብቻም አይደለም፣ መስከረም 2013 ዓ•ም አካባቢ የክልሉ መረበሽ ጫፍ ከመድረሱ የተነሳ የአጎራባች ክልሎች (ከአማራ ክልል በተጨማሪ የጋምቤላ፣ የሲዳማ እንዲሁም የደቡብ ክልል ልዩ ኃይሎች) ወደ አካባቢው በማቅናትና በክልሉ ተቋቁሞ በነበረው ኮማንድ ፖስት ስር በመሆን ሠላም ማስከበር ሥራ ሲሰሩ መቆየታቸው የሚዘነጋ አይደለም።

ዛሬ የምንመለከተው ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ትናንት ነገሮችን ልብ ማለት ባልቻሉ ልጆቹ፤ ለሶስተኛ ወገን ሀሳብ በተገዙ የራሱ ወገኖች ሲተራመስ ነበር። ምስኪኑ የክልሉ ሕዝብ በማያውቀው ጉዳይ ከመጎዳቱም ባለፈ እንደ ጎጂ ተደርጎ እዚህ መሀል ከተማ፣ መዲናዋ ድረስ ሲወራበት ነበር። ሕዝቡን የማይወክሉ ሕዝቡን የማይወክል ስራን በመስራታቸው ምክንያት የክልሉ ሕዝብ በሌላው ላይ ጦር እንደ መዘዘ ተደርጎ እስኪወራ ድረስ በክልሉ ሠላም አልነበረም።

ዛሬስ ምን ለውጥ አለ ስንል ከክልሉ ሠላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ የፀጥታ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አሰም የሱፍ ጋር ቆይታ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን ፦ በቅድሚያ እርሶ የሚመሩትን ዘርፍ ዐቢይ ተግባር ቢገልፁልን።**

**አቶ አሰም የሱፍ፦** *እኔ የምመራው ዘርፍ የሰላምና ጸጥታ ዘርፍ ነው፡፡ ዘርፉ እንደ ተቋምም ሆነ ሠላምና ፀጥታ ዘርፍ ተልእኮው በክልሉ ዘላቂ ሠላም መገንባትና የማኅበረሰቡን ደህንነተ በተሟላ መልኩ ማስጠበቅ ነው።*

**አዲስ ዘመን፦ ተልእኮው ይህ ከሆነ ይህንን ተልእኮውን በአግባቡ ሲወጣ ቆይቷል ይላሉ?**

**አቶ አሰም የሱፍ፦** *አዎ፣ ሲወጣ ቆይቷል፤ እየተወጣም ነው። ይሁን እንጂ መሰናክሎች የሉም ማለት አይደለም፤ እንደ ማንኛውም የአገራችን ክፍሎች እኛም ጋ የጸጥታ ችግሮች ተከስተው ነበር። በተለይ ያለፉት አራት ዓመታት ብዙ የተፈተንበት፤ ወደ ድርድርም የገባንበትና ውጤትም ያስመዘገብንበት ነው።*

*በተለይ ይህ ክልል ራሱ የለውጡ አካል ስለነበር፤ ለውጡን ተከትሎ ያኮረፉ ኃይሎች ጠመንጃ ወደ መተኮስ ነው የገቡት። ለማደናቀፍ ጥረት መደረጉ ስለማይቀር፣ ይህ ይጠበቅ ነበር። እንደ ሌሎች አካባቢዎች ሁሉ እዚህ እኛ ክልልም የሆነው ይኸው ነው። በተለይ በሶስት ዞኖችና በአንድ ልዩ ወረዳ ውስጥ ችግሮች ተከስተው ነበር። በሁለት ዞኖች ከፍተኛ ውድመትና ሰብአዊ ቀውስ ደርሷል። መፈናቀልም ነበር።*

*ይህ ያኮረፈ ኃይል፣ ለውጡን ለማደናቀፍ በማሰብ በተነሱ ኃይሎች በተቀሰቀሰ እሳት ምክንያት በርካታ ጉዳቶች ደርሰዋል። ንብረቶች ወድመዋል። የሰው ልጅ ሕይወት ጠፍቷል። ባለፉት ስድስት የለውጥ (በተለይም ከወደዚህ ያሉት አራት) ዓመታት ከፍተኛ ቀውስ ነበር። ከአሶሳ ዞን ውጪ በሁሉም ዞኖች ማለት ይቻላል ያኮረፈው ቡድን፤ የለውጡ ተቃዋሚ ኃይል የፈጠራቸው የፀጥታ ችግሮች ነበሩ።*

*ከላይ እንዳልኩህ፣ ያኮረፈው ቡድን፣ ጥቅሜ ቀረብኝ ያለው ክፍል፣ ፅንፈኛው በፈጠራቸው ግጭቶች በሚያሳዝን ሁኔታ የዜጎች ሞት፣ መፈናቀልና የንብረት መውደም ተከስቷል። መተከልና ካማሺ ብቻ ከ400ሺህ በላይ (ከአጠቃላይ ነዋሪው ሕዝብ ከ70% በላይ) ሕዝብ የተፈናቀለ ሲሆን፣ ወደ ሱዳን እስከ መሰደድ ድረስ የሄዱ አሉ። በማኦ-ኮሞ፣ አሶሳ ዙሪያም እንደዛው የሕዝብ መፈናቀል ነበር። ማክሸፍ ተቻለ እንጂ፣ ከሶስተኛ ወገን ተልእኮ ወስደው በነበሩ አካላት የተደራጀ ስራን በመስራት ክልሉን የማፍረስ ስራ ነበር ሲሰራ የነበረው። በተለይ በቤኒን ሲንቀሳቀስ የነበረው ቡድን ከሸኔና ፅንፈኛው የአማራ ኃይል ድጋፍ ይደረግለት ነበር። አሁን እነዚህን ሁሉ፤ ሳያውቁት ወደ ወገናቸው ሲተኩሱ የነበሩትን ሁሉ ወደየ አካባቢያቸው መመለስ፤ ወደ ልማት ስራዎች ማስማራት ተችሏል። የከፍተኛ አመራሮች ቡድንና የፀጥታ አካላት ባደረጓቸው የማወያየት ተግባራትም በሕብረተሰቡ መካከል መተማመን ተፈጥሯል።*

*ከኦሮሚያ ክልል የተፈናቀሉም ነበሩ። እነሱም ወደ እዚህ የመጡበት ሁኔታ ነበር። ባንባሲ ወረዳ ላይ መጠለያ ተደርጎ ሰፍረው ነበር። በከፊል እየተመለሱ ነው።*

*ከሱዳን፣ ከቡሩንዲ - - - ሁሉ ተፈናቅለው ወደዚህ በመምጣት ከ6 ዓመት በላይ የኖሩ ነበሩ። አሁን ሄደዋል። አሁንም ያሉ ሱዳናውያን አሉ። ይህ በራሱ ለክልላችን ድርብ ችግር ሆኖ ነው የቆየው። ቢሆንም ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን እንደ አገርም፣ እንደ ክልል አመራርም ኃላፊነታችንንና የሚጠበቅብንን እየተወጣን እንገኛለን።*

**አዲስ ዘመን ፦ በእናንተ ግምገማ፣ ይህ ቡድን አሁን በምን አይነት ደረጃ ላይ ነው ያለው?**

**አቶ አሰም የሱፍ፦** *በቅድሚያ ያኮረፈ ቡድን፣ ከዚህ ክልልም፣ ከዚህ ክልል ውጪም ተደራጅቶ ይህንን ክልል ሊያፈርስ እንደ ፈለገ ተደረሰበት። ይህ የተደራጀ፣ አኩራፊ ቡድንም ከሁለተኛና ሶስተኛ ወገን ክልሉን የማፍረስ ተልእኮ የተሰጠው፤ ትእዛዝ የተቀበለ መሆኑም ተደረሰበት። በጉዳዩ ላይ ሙሉ ግንዛቤ ተያዘ። በተደረሰበት ግንዛቤ ልክም ክልሉ መፍረስ እንደ ሌለበት፤ ያኮረፈው ኃይልም ያልተገነዘበው ነገር እንዳለ መረዳት እንዳለበት፤ ወደ ወገኑ ለመተኮስ ጫካ የገባው ቡድንም በማያውቀው ጉዳይ ወገኑ ላይ እየተኮሰ፤ ወንድሙን እየገደለ እንደሆነ እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ስለ መሆኑ መግባባት ላይ ተደረሰ። በዚሁ መሰረትም ወደ መነጋገሩ ስራ ተገባ። በአራቱም አቅጣጫ ድርድሩ ተጀመረ። ከክልሉ ውጪ፤ ውጭ አገር (ሱዳን) ከሄዱት ጋር ሳይቀር ለውይይት ተጋበዙ። ከአጎራባች ክልሎች ጋር በጋራ መስራቱም ተጠናክሮ ቀጠለ።*

*በአመራሩ በኩል፣ ከፌደራል ጀምሮ ለሰላም ሲባል ከፍተኛ መስዋእትነት ተከፍሎ በድርድር ወደ ስምምነት በመምጣት ወደ ሰላም ተመልሰዋል። ፕሬዚዳንቱ ሳይቀሩ፣ አመራሩ ኃላፊነት ወስዶ፣ ጫካ ድረስ በመሄድና በመነጋገር፤ በማመንና በማሳመን፤ የመተማመን ስራዎች ተሰርተው ሰላም ወርዷል። ከነ መሳሪያቸው ነው የተመለሱት። በሰላምም መሳሪያቸውን አስረክበዋል፤*

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ምንም አይነት ...

ከገጽ 6 የዞረ

ተረክበናቸዋል።

አሁን ወደ ልማት ገብተዋል። በተለያዩ ዘርፎችም ተሰማርተው፤ ተደራጅተው ወደ ስራ በመግባት ውጤታማ እየሆኑ ነው። እርሻ፣ ወርቅ፣ ሸቀጣሸቀጥ ንግድ ወዘተ ከተሰማሩባቸው መስኮች መካከል ናቸው።

እስከ ባለፈው ሚያዝያ ወር ብቻ በክልሉ የሰላም ጥሪን ተቀብለው የገቡ ከስምንት ሺህ በላይ የቀድሞ ታጣቂዎች በተለያዩ ሥራዎች ተሰማርተው ይገኛሉ።

ወደ ስራ የተሰማሩት ዝም ብለው አይደለም። ክልሉ ባመቻቸው፣ ባዘጋጀውና በፈጠረው እድል ወደ መጠቀም ከመሄዳቸው አስቀድሞ ተሀድሶ እንዲወስዱ ተደርገዋል። በተሀድሶው መሰረትም ወደ ነበሩበት የስነልቦና ሁኔታ እንዲመለሱ፤ ከማህበረሰቡም ጋር በቀላሉ እንዲዋሀዱና እንዲደራጁ ተደርጓል።

እነዚህን ወገኖች ለመጥቀም ሲባል እንደ ክልልና ሕዝብ ብዙ ዋጋ ተከፍሏል። ከሌሎች ልማቶች በመቀነስ 46 ትራክተሮች፣ 26 የወርቅ ማሽኖች፣ ባጃጅና ሌሎችም ተገዝቶላቸው ነው ወደ ስራ የገቡት። ይህ ሁሉ የተደረገው በእቅድ ከተያዙት የልማት ስራዎች ተቀንሶ ነው። በአጠቃላይ ከልማት ላይ ተቀንሶ ከ288 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን :- አሁን ክልሉ ሠላም ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** አዎ፣ አንፃራዊ ሠላም አለ። በተለይ ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ሙሉ ለሙሉ በክልላችን በሠላም ወጥቶ በሠላም መግባት የተቻለባቸው ዓመታት ናቸው። በአሁኑ ወቅት በክልሉ ምንም አይነት የፀጥታ ችግር የለም።

**አዲስ ዘመን :- አንፃራዊ ሠላም የሚለው እንዴት ይገለፃል?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** አንፃራዊ ሠላም አለ ሲባል ሙሉ ለሙሉ ስጋት የለም ማለት አይደለም። ሁኔታዎችን በቅርብ መከታተል ያስፈልጋል። አንፃራዊ ሠላም አለ ሲባል ሙሉ ለሙሉ ወደ ድሮው፣ ወደ ነበረበት ተመልሷል ማለትም አይደለም። ክልሉና የክልሉ ሕዝብ ከነበረበት ሁከት፣ ረብሻና የፀጥታ ስጋት ወጥቶ ወደ ልማት የተመለሰበት ሁኔታ ነው ያለው ለማለት ነው። ሁኔታዎችን ወደ ሠላም ለማምጣት ሲጀመርም ቅድሚያ ተሰጥቶ የነበረው ሠላሙን ላጣው፤ ለተፈናቀለው ማኅበረሰብ ቅድሚያ በመስጠት፤ የተፈናቀሉትን ወደ ቀያቸው በመመለስ ነበር። ከአጎራባች (ለምሳሌ ከኦሮሚያ) የመጡ ተፈናቃዮችንም ወደ መጠለያ በማስገባትና አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንዲያገኙ በማድረግ ነው። እነዚህ ወገኖች ወደ ክልልና አካባቢያቸው እንዲመለሱም እየተደረገ ይገኛል።

አሁን በክልሉ የትም ቦታ መንቀሳቀስ ይቻላል። ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውና የፀጥታ ስጋት የነበረባቸው አካባቢዎች ሳይቀሩ ወደ ስራ ገብተዋል፤ አካባቢዎቹ ፀጥታ ሰፍኖባቸዋል። የመንቀሳቀስ ችግር የለም። የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ በማስፈርና በአካባቢው የተሰማሩ ባለሃብቶችን ዘላቂ ደህንነት በማስጠበቅ አካባቢውን የልማት ኮሪደር የማድረግ ስራ እየተሰራ ነው። ያ ማለት ግን አሁን ምንም ችግር የለም ማለት አይደለም። ችግሮች አሉ።

**አዲስ ዘመን:- ችግሮች ካሉ ምን ምን እንደ ሆኑ መግለፅ ከተቻለ ቢገልፁልን?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** እንደሚታወቀው እንደ አገርም ሆነ እንደ ክልል ሠላም ለማስፈን የአንድ አካባቢ ሠላም መሆን ብቻውን በቂ አይደለም። የአንድ አገር ሠላም መሆን የሚረጋገጠው በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ሠላም ሲሰፍን ነው። ጉዳዩን ወደ ክልሎችም ስናመጣው ያው ነው። ማለትም ሁሉም ክልሎች ሠላም ካልሆኑ አንድ ክልል ብቻውን ሠላም መሆን አይችልም። ምን ማለት ነው፣ የእኛ ክልል የውስጥ ሠላም መኖር ብቻ ክልላችንን ሠላም አያደርገውም። ለእኛ የተሟላ ሠላም የአጎራባች ክልሎች ሁሉ ሠላም መሆን ያስፈልጋል። አጎራባቻችን አማራ ክልል ሠላም ከሌለ እኛ ጋ ሠላም አለ ማለት አይቻልም። አዋሳኛችን ኦሮሚያ ክልል ሠላም ከሌለ የእኛ ሠላም መሆን ብቻ የተሟላ ሠላም እንዲኖረን ሊያደርገን አይችልም። ለዚህ ነው ችግር አለ የምንለው። እንደ ልብ ወደ አጎራባች፣ አዋሳኝ ክልሎች ገብተን መውጣት አልቻልንም፤ አንችልም። ዳንጉር አካባቢ ችግር አለ፤ ፅንፈኛው እየገባ ይወጣል። በመተከልም እንዲሁ እየገባ የሚወጣበት ሁኔታ አለ።



**ፕሬዚዳንቱ ሳይቀሩ፣ አመራሩ ኃላፊነት ወስዶ፣ ጫካ ድረስ በመሄድና በመነጋገር፤ በማመንና በማሳመን፤ የመተማመን ስራዎች ተሰርተው ሰላም ወርዷል**

ወደ አማራ፤ ወደ ኦሮሚያ ክልል እንደ ፈለጉ መሄድ አይቻልም። ይህ፣ የክልላችንን ሕዝብ እንቅስቃሴ የሚገድብ ፀረ-ሠላም ተግባር ደግሞ ከሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ ሸቀጦችን ከማምጣት ጀምሮ ምን ያህል ችግር እንደፈጠረና ሕዝቡን ለኑሮ ውድነት እየዳረገ መሆኑ እየታየ ነው።

አንድ ሕዝብ የገበያ መረጋጋት፣ ሸቀጦችን የመገብየት፣ የማስገባት፣ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በነፃነት የመንቀሳቀስ ወዘተ መብቱ ከተገደበ ያ ማሕበረሰብ የተሟላ ነፃነት፤ የተሟላ ሠላም አለው ማለት አይቻልም። የተሟላ ነፃነት፤ የተሟላ ሠላም አለ ማለት የሚቻለው ከነጎረቤቶቻችን ሠላም ስናገኝ፤ ሠላም ሲኖር፤ በሠላም ወደ ጎረቤት ክልሎች ሄደን ስንመጣ ነው። ያ ከሌለ እንደ ሰላም እጦት ነው የሚቆጠረው። ያ ሕዝብ የሚበላው ካጣ አሁንም ችግር ነው ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን:- ከችግሮች አኳያ አሁን ያለውን ሁኔታ ባጭሩ መግለፅ ይቻላል?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** ይቻላል። እንዳልኩህ፣ አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ችግሮች አሉ። አጎራባች ክልሎች አካባቢ ችግሮች አሉ። በኦሮሚያ ሸኔ እየተንቀሳቀሰ ነው። እየገባ የመውጣት ሁኔታ አለ። አማራ አካባቢም ችግርች አሉ። ፅንፈኛው ይንቀሳቀሳል። ሕብረተሰቡን እያጠቁ የሚመስሉ ሁኔታዎች አሉ። አሁንም ኢመደበኛ አደረጃጀቶች አሉ። እርግጥ ነው ቅድመ መከላከል ስራ እየተሰራ ነው። ግን በቂ አይደለም። ቤንኒሻንጉል ጉሙዝ እንደ ክልል ነፃና ሠላማዊ ይሁን እንጂ ወደ አጎራባች ክልልች በነፃነት መመላለስ አይችልም። ወደ አማራና ኦሮሚያ ክልሎች መንቀሳቀስ ከባድ ብቻ ሳይሆን አይቻልም። በጋራ መስራትን የሚጠይቁ ስራዎች አሉ። እንደ አገር የፌደራል መንግሥትን ስራዎች የሚፈልጉ ስራዎች አሉ። የመከላከያን ስራ የሚፈልጉ ስራዎች አሉ። የኃይል ርምጃ የሚፈልጉ ስራዎች አሉ። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት የሚፈልጉ ስራዎች አሉ።

**አዲስ ዘመን :- ከክልሎች፣ በተለይም ከአጎራባች ክልሎች ጋር በሠላም ዙሪያ አብራችሁ ከመስራት አኳያ ያላችሁን ግንኙነት ቢገልፁልን ?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** ከአማራ፣ ከኦሮሚያ ጋር ግንኙነቶች አሉን። ያም አንፃራዊው ሠላም እንዲመጣ አግዟል። ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በሠላም ሚኒስቴር የሚመራ፣ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ፎረም አለን። የጋራ ስብሰባዎችን፤ ውይይቶችን እናደርጋለን። በዛ ፎረም ላይ እየተገናኘን እንመክራለን። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን የመስራት ነገርም አለ። ይህ ሁሉ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን :- እንደ አጠቃላይ ምን ቢደረግ ጥተሩ ነው ይላሉ?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** አሁን ከዛ ብንወጣም ለአራት ዓመት በከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው የቆየነው። ሰላም ማጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እናውቀዋለን። ብዙ ነገሮች ሊደረጉ ይችላሉ። አንዱ ጋ ሠላም ከሌለ ሌላው ጋ ሠላም ሊኖር እንደማይችል በመገንዘብ አጎራባች ክልሎች አብረው፤ በጋራ ሊሰሩ ይገባል። የአንዱ ክልል ሠላም አለመሆን ለሌላው ክልልም ሠላም አለመሆን ምክንያት ነውና በአንዱ ክልል ችግር ሲፈጠር ያንን ችግር ለመፍታት ተናቦ፣ ተግባብቶ፣ ተባብሮ፣ መረጃ ተለዋውጦ በጋራ መስራት ይገባል። እኔ ጋ ችግር የለም ብሎ መቀመጥ ምንም ፋይዳ የለውም። አያስኬድም። እንደ ብልፅግናም ያለው አቋም ይሄ ነው፤ የጋራ ሠላም ላይ መስራት ነው የሚገባው።

**አዲስ ዘመን :- የፌዴራል መንግስት የነበረውን እገዛ እንዴት ይገልጹታል ?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** እርግጥ ነው። በክልላችን ሰላም ማስፈን የቻልነው በአገር መከላከያ ኃይል ነው። ከመከላከያ ጋር እጅና ጓንት ሆነን በመስራት ነው። የፌደራል መንግስትን አቅጣጫ ተከትለን በመስራታችን ነው ለውጤት የበቃነው። ነገር ግን፣ አጎራባች ክልሎች ጋ ችግር ሲኖር ቤኒሻንጉል አማራ ክልል ሄዶ ስርዓት ማስያዝ አይችልም። ኦሮሚያ ክልል ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ገብቶ ሠላም ሊያመጣ አይችልም። በእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ ችግሮችን ሊፈታ የሚችለው፤ ጣልቃ ሊገባ የሚችሉት ፌደራል ፖሊስና እና መከላከያ ሰራዊት ናቸው። ይህ ሊሆን፣ ሊደረግ ይገባል። በአጎራባች ክልሎች አካባቢ አሁንም የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች አሉ።

እነዚህን በኃይል ማስቆም ይገባል። ኃይል ያስፈልጋል። የኃይል ስራ የሚፈልጉ ጉዳዮች አሉ። የኃይል ርምጃን የግድ የሚሉ እንቅስቃሴዎች አሉ። ይህንን ማድረግ የሚችለው፤ ሕገመንግሥታዊ መብትም ያለው ደግሞ መከላከያ ነው።

**አዲስ ዘመን :- በመጨረሻም ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ አሰም የሱፍ:-** የተገኘውን አንፃራዊ ሠላም ለማስቀጠልም ሆነ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ተቋማዊ ስራዎች በሚገባ መሰራት አለባቸው። ፖሊስ፣ መከላከያ እና ሌሎች የሚመለከታቸው ሁሉ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መስራት አለባቸው። የሕዝብ አደረጃጀቶችን (ሴቶች፣ ወጣቶች ወዘተ) ማጠናከር ያስፈልጋል። ማሕበረሰቡ ራሱን እንዲጠብቅ ማድረግ ያስፈልጋል (ኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ሊጠናከር ይገባል)።

የተገኘውን አንፃራዊ ሠላም ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ የአካባቢው ማሕበረሰብ ከዚህ በፊት ሲያደርግ የነበረውን ትብብር የበለጠ አጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል። ባለፉት አራት ዓመታት በፀጥታ ችግር ውስጥ የቆየው የክልላችን ሕዝብ በጋራ ባደረገው ጥረት ወደ አሁኑ አንፃራዊ ሠላም መምጣት ችሏል። ይህ አሁንም የበለጠ ተጠናክሮና ሕዝባዊ መሰረት ይዞ መቀጠል አለበት።

ለሁሉም ጦርነት አክሳሪ እንጂ አትራፊ አለመሆኑ፤ ለማንም እንደማይጠቅም፤ ሁሉንም ወገን እንደሚጎዳ፤ አገርና ሕዝብን ወደ ኋላ እንደሚያስቀር መንገር፤ ትምህርት መስጠት አለበት። ሁሉም ይህንን እንዲረዳ መሰራት ያለበት ሁሉ መሰራት አለበት። ትምህርት ያስፈልጋል። ውይይት ያስፈልጋል። የወጣቶች ክበባት መጠናከር አለባቸው። የሠላም እናቶችን ማሳተፍ ያስፈልጋል። የሠላም እሴቶችን መገንባት ያስፈልጋል። በክልሎች የአመራር ለአመራር ግንኙነቶች መጠናከር አለባቸው። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ መስራት ያስፈልጋል። መከላከያና የፀጥታ ኃይሉ በጋራ እየሰሩት ያለው የሠላም ማስከበር ስራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። እነዚህና ሌሎችም በሚገባ ከተሰራባቸው ዘላቂ ሠላም ይኖራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለ ሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ አሰም የሱፍ፡-** እኔም እዚህ ድረስ መጥታችሁ ለአስተያየት ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ነፃ ሃሳብ

## ሀገርን መሀል አድርገን፤ለሕዝብ ቅድሚያ ሰጥተን እንመካከር

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሰላምና አንድነት ግድ የሚላት ጊዜ ላይ ነን:: በተለያዩ ጊዜ የተነሱ ፖለቲካዊና ብሄር ተኮር እሳቤዎች የመከራ ገጽ አላብሰዋት ሰንብታለች:: ከጦርነት ወደጦርነት በሆነ የፉክክርና የይዋጣልን እልህ ለማንም በማይበጅ የብኩርና ግፊያ ውስጥ እልፍ ዓመታትን በሞትና በጉስቁልና ውስጥ ከርመናል:: በሰላም ስለሰላም መነጋገርና መግባባት አቅቶን ጠመንጃ ስንወለውልና ካራ ስንስል ከዛሬ ማለዳ ላይ ደርሰናል::

የሚያግባቡን ብዙ እያሉ እንደመዳፍ በጠበበ የልዩነት አውድ ላይ ተጠምደን ጣት ስንቀሳሰር፣ የታባክ ምናባክ ስንባባል ከሀገር ያገዘፉንን፣ በታሪክ ያደመቁንን ጳዐዳ መልኮቻችንን ከልለናል:: ከፊታችን ወዳለና በጋራ ወደተበጀ እውነት ከማየት ይልቅ አንሰውና ቀንጭረው አልታይ ወዳሉ የልዩነት መስኮች እያስተዋልን ኢትዮጵያዊነትን ሸረንዋል:: ወንድማማችነትን ዘርቶ ባበቀለ ሩህሩህ ልብ ላይ፣ ኢትዮጵያዊነትን ባጸደቀ ለም አእምሮ ላይ የዘረኝነት መርዝ ረጭተን ከተሲያት የከለሉንን፣ ከውርደት የታደጉንን ዋርካዎቻችንን አጠውልገናል::

ባልነበረ ተረት ተረት፣ በነጣጣይ እኩይ ትርክት ትውልዱ እንዲሰጋጋ እና እንዲፈራራ ጥላቻን አጋብተንበት ሆደ ባሻ እንዲሆን አድርገነዋል:: በጥላቻ ተቧድነን፣ ለጦርነት ተዛዝተን የነጻነቷን ምድር አስጊ፣ የምህረት እጆችን ገዳይ አድርገን ቀይረናቸዋል:: ስለሌላው ግድ የሚለው ሀበሻነት፣ የጣሊያንን ምርኮኞች አቅፎና ደግፎ በክብር ወደቀያቸው የሰደደ ኢትዮጵያዊነት በወንድሞቹ ላይ እንዲጨክን በዘረኝነት መርዝ አስክረንዋል:: ሀ ሲል ፊደል የቆጠረው ትውልድ፣ አቦጊዳ ሲል ግዕዝ ያጠናው ብላቴና በዝሆኖች ግፊያ ያለስራው አበሳ ቆጣሪ ከሆነ ሰንብቷል:: መካሪና ገሳጭ፣ አስታራቂና ዘካሪ ሽበታም ጠፍቶ በትዕቢተኞች በለው በለው ፍቅር የከሰመበትን አዲስ ማንነት ወርሰናል::

ሰላምና ፍቅር አብበው ያፈሩባት፣ ነጻነትና ሉአላዊነት አፍ የፈቱባት ምድር፣ ክብርን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ለዓለም ያስተዋወቀች ጦብያ ምንም እንደሌለው በሰላም ርሀብ፣ በፍቅር ድርቀት ስትሰቃይ እንደማየት የሚያም የለም:: ለአብነት እነዚህን ጠቀስኩ እንጂ ጉዶቻችን ብዙ ናቸው:: ከትላንት ወደዛሬ የመጡ፣ ዛሬ ላይ ወልደን ያሳደግናቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የብሔር፣ የወሰን ትርክቶች ብዙ ናቸው:: ያለን ሳይበቃን አዲስ መከራ እየፈጠርን እንደ ጃርት ገላ በመላ ሰውነታችን ላይ የመከራ ቀስትን ታጥቀናል::

መፍትሄው ምንድ ነው? መልካሙ ነገር ሁሉም ችግር መፍትሄ ያለው መሆኑ ነው:: መፍትሄ ካለው እኛ ለምን መፍትሄ አጣን? መከራዎቻችንን ወደጦርነት እና ወደሞት ሲወስዱን ስለምን ዝም አልን? ዘረኝነት ከኢትዮጵያዊነት በልጦ ዋጋ ሲያስከፍለንና ታሪካችንን ሲቀማን እንደምን አስቻለን? በጋራ ሀገር እና ታሪክ ላይ እኔነት አብቦ እኛነትን ሲያጠወልግብን ምን ከጀልን? የሚሉ እና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች መነሳታቸው ግድ ነው:: እኛና ችግራችን ለምን እንዳልተግባባን፣ ችግር እኛን እኛም ችግርን አፍቅረን ለምን እንደኖርን አሁን እነግራችኋለው:: በእርግጥ አዲስ ነገር አልነግራችሁም የምታውቁትን ግን ደግሞ ችላ ያላችሁትን እውነታ ነው የማስታውሳችሁ::

ዓለም ከዘመነበት የስልጣኔ መነሻዎች መሀል ‹ሁሉም ችግር መፍትሄ አለው፣ ችግሩን በፈጠረው አእምሮ መፍትሄ ማምጣት አይቻልም› የሚሉት ምክረ ሀሳቦች በወርቅ ሚዛን የሚመዘኑ እጅግ ትርፋማዎቹ ናቸው:: ሁሉም ችግር መፍትሄ አለው ስንል መነጋገርንና መደማመጥን ላስቀደመ አእምሮ ነው:: ልዩነቱ ላይ ሳይሆን አንድነቱ ላይ ላተኮረ ማኅበረሰብ ነው:: ከጦርነት በፊት ሰላምን ለማምጣት ፖለቲካቸውን አስፍተው፣ ልባቸውን አግዝፈው ስለሀገርና ሕዝብ ሰላም ለማውረድ ለተስማሙት ነው:: ሁሉም ችግር መፍትሄ አለው ሲባል.. ልዩነትን ለውበት አንድነትን ለኃይል በመጠቀም መርህ ውስጥ ስላለው ልማትና እድገት፣ ዘመናዊነትና ስልጣኔ እያወራን ነው:: ኢትዮጵያዊነትን ባስቀደመ ሀገር ማለት ሰው፣ ሰው ማለት ሀገር ነው በሚለው ሊቀ ሀሳብ ለተመራ ነው::

ችግሩን በፈጠረው አእምሮ መፍትሄ ማምጣት አይቻልም ሲባል ደግሞ ችግርና ሰላም አብረው የሚሄዱ እንዳይደሉና ስለ ሰላም በሰላም መወያየትና በመደማመጥ ግድ እንደሚል እያስረዳን ነው:: የእኛ ሀገር የችግር አፈታት ዘዴ ከችግር ወደችግር ነው:: አባባሽ ነገሮችን ከመፍጠር ባለፈ መፍትሄ ተኮር መሆኑ እምብዛም ነው:: ችግሩን በፈጠረው አእምሮ ሰላም መፍጠር አይቻልም:: ስለጦርነት እያወራን፣ ስለዘረኝነት እየሰበክን እንዴት ነው አብሮነትን የምናጸናው? ገዳይና ሟች ያሉበትን የብቻ ትርክቶችን እየፈጠርን እንዴት ነው ተከባብረንና ተቻችለን የምንኖረው?

ሁሉም ችግር መፍትሄ አለው ስንል ሀገርን መሀል አድርገን ስንወያይና ለሕዝብ ቅድሚያ ሰጥተን ስለአብሮነት ስንመካከር ነው:: ላሉብን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍትሄ ለማምጣት ከነውጥ ፈጣሪነት ወጥተን ወደለውጥ ፈጣሪነት መሸጋገር አለብን:: ሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ሰላም ትፈልጋለች:: ሕዝባችን፣ ትውልዱ ፍቅር ይሻል:: ልማቱ፣ እንስሳቱ፣ አየሩ፣ ቀዬው ሞት ሰልችቶታል:: እውነቱ ቃታ በመሳብ ዝለናል:: እጆቻችን በመግደልና በመሞት ሻክረዋል:: እስኪ ደግሞ ጊዜውን ለሰላም እንልቀቅ:: እስኪ ደግሞ በሰላም ስለሰላም የሞት ደመናችንን ገፈን የተስፋ ጣይ እንፈንጥቅ::

**ኢትዮጵያን የማዳን ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ነን:: የምንድነውም ሆነ የምናድነው ደግሞ በሀሳብ ነው:: ጠመንጃ ሀገር አያድንም:: ጦርነት ሰላም አያመጣም:: ቂም በቀል የፍቅርን ደመና ይጋርዳሉ እንጂ ፍቅር አያዘንቡም**

የምድር ውበት ሰላም ናት:: የሰው ልጅ ዓርማው ፍቅር ነው:: ሰላምና ፍቅር በአንድ ሀገር ላይ እንደሉአላዊ ሰንደቅ ዓላማ የክብር ደፎች ናቸው:: ሰንደቅ ለአንድ ሀገር መጠሪያ ከዚያም ሲገዝፍ የክብርና የአይነኬ ወሰን ነው:: ሰላምና ፍቅርም በሕይወት ላይ እንዲሁ ናቸው:: ሰላም ከሌለን ምንም ነገር እንዳይኖረን ሆነን የተበጀን ነን:: ፍቅር ከራቀን እንደሚንሿሿ ናስ በማይሰማና በማይማርክ ሰውነት ውስጥ ለመኖር እንገደዳለን:: መታወሻችን ሞትና ጉስቁልና፣ ጥላቻና ዘረኝነት ሆኖ ትውልዱን ይሻገራል:: መታሰቢያችን ከምድር እንዳይጠፋ በክፋት ቀድሞ ተጠቃሾች እንድንሆን የክብር ቀርቶ የነውር ሀውልት ይቆምልናል:: እስኪ ስለፍቅር እንሙት:: እስኪ ስለሰላምና ስለወንድማማችነት እንድከም::

የዓለም የጀግንነት ኒሻን ያለው ሞቶ በመግደል ውስጥ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሁሉ ሰላም በማወጅ ውስጥ ነው:: ጀግና ልብ ኖሮ ማኖርን እንጂ ገሎ መሞትን አያውቀውም::፡ ዘመናዊነትና ስልጣኔ ጥሎ መውደቅን አያውቁትም:: ከእኛ ለእኛ በሆኑ ገዳይ ነውሮቻችን ውስጥ ነን:: በየትም በሌሉ በእርስ በርስ ሽኩቻ ስር ከወደቅን ቆይተናል:: እስኪ ማን አጠቃን? ጣሊያን ቻለን? እንግሊዝና ዝያድባሬ ቻሉን? ግብጽና ጉርድፎች አሸነፉን? እርስ በርስ ነው እየተበላላን ያለነው:: እርስ በርሳችን ነው እየተናናቅን ያለነው:: ለዛም ነው ሞታችን ያላባራው:: ለዛም ነው መከራችን መጨረሻ ያጣው::

ትርፍ በሌለው በአንድ አይነት ሰጣ ገባ ውስጥ እስከመቼ እንደምንዘልቅ አላውቅም:: በእርቅና በምክክር ለዛውም በጊዜ የለበስነው የጥላቻ ካባ እስካላወለቅን ድረስ ራሳችንን በኢትዮጵያዊነት ለዛ ለማየት ዋጋ መክፈላችን የማይቀር ነው:: ይሄ ሁሉ ከመሆኑ በፊት አስታራቂና መካሪ ሆነው በመጡ እንደ ብሄራዊ ምክክር ባሉ ሕዝባዊ መድረኮች ላይ መወያየትና መነጋገር ያስፈልጋል:: በፍቅርና በይቅርታ፣ በአብሮነትና በኢትዮጵያዊነት ካልሆነ በእልህና በጥላቻ፣ በበቀልና በቂም እድፎቻችን አይጠሩም:: ካባዎቻችን አይወልቁም:: ዘረኝነት ከልሷት እንጂ፣ ተረት ተረት ሸፍኗት እንጂ በሁላችንም ልብ ውስጥ ኢትዮጵያዊነት አለ:: እውነታችን እንዲታይ ጭንብላችንን እናውልቅ::

በሰከነ ልቦና ስላላየናቸው እንጂ ችግሮቻችን ቀሊሎች ናቸው:: በመነጋገር ስላልሄድንባቸው እንጂ ልዩነቶቻችን ለመገፋፋት የሚያበቁን አልነበሩም:: በሰላም ለሰላም ከበረታን ከአቅማችን በላይ የሚሆን ምንም የለም:: የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን ከዓመታት እንቅስቃሴው በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያውን የአጀንዳ ልየታ መርሀ ግብሩን እያከናወነ ይገኛል:: ሳምንት በሚቆየው እና ከ2500 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙበት ይሄ መድረክ ተስፋ ሰጪ የሆኑ፣ የሀገራችንን መጻኢ እድል የሚወስኑ የሰላምና የአብሮነት ሀሳቦች እንደሚንሸራሸሩበት ይታመናል::

በሂደቱ አዲስ አበባን ወክለው የሚሳተፉ ተወካዮች ይመረጣሉ፣ የከተማው የምክክር ጉባኤ ይሰየማል:: ሌሎች በመርሀ ግብሩ የተቀመጡ እንደቅደም ተከተላቸው የሚሄዱበት መድረክ ነው:: ሰባቱንም ቀናት አዋጭና አትራፊ በሆኑ ክንውኖች በኩል እንደሚሻገር የተገለጸ ሲሆን ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ ሀገር በማዳን ስራው ላይ መሳተፍ ውዴታችን ሳይሆን ግዴታችን ይሆናል::

ሀገራችንን ለመታደግ ውይይት እንደቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ መስፈርት ነው:: በውይይት የማይፈታ ምንም ነገር የለም:: ሀሳብ ላለው ልብ ሁሉም ችግር ሀገር ለመቀየር መልካም አጋጣሚው ነው:: ሀሳብ ለሌለውና በእልህ ለሚኖር አእምሮ ግን ሁሉም ልዩነት ወደጦርነት የሚወስዱ ናቸው:: በእኛ ሀገር ነባራዊ ሁኔታ ችግር ፈጣሪነት እንጂ ችግር ፈቺነት ጎልቶ አይስተዋልም:: የምንባደነው ለጠብ ነው:: ጎራ የምንፈጥረው ለግጭት ነው:: ለሰላምና ስለሰላም ጎራ ፈጥረን አናውቅም:: እኚህ ልምምዶቻችን ከትላንት ዛሬ ላይ አርፈው ነገንም ሊቀሙን እያኮበኮቡ ነው..በቃ ልንል ይገባል::

በሀሳብ የዳበረ ፖለቲካ፣ ለመነጋገርና ለመግባባት ደጃፉን የከፈተ የለም:: ለዛም ነው ኮሽ ባለ ቁጥር ጠመንጃ የምናነሳው:: ለዛም ነው ትንሸዋ የሀሳብ ጥበት ግዙፍ ልዩነትን ፈጥራ እልቂትና ውድመት የምታደፈርሰው:: ኢትዮጵያዊነትና ግብረገብነት በሌለበት፣ ሰላምና ወንድማማችነት ባልተረጋገጠበት ሀገር ላይ ሀገርና ሕዝብ ትውልድና ታሪክ ምንድነው? ጨዋነትና መከባበር፣ መቻቻልና መተቃቀፍ በሌሉበት ፖለቲካ ስር ምን የተስፋ ጣይ ይፈነጥቃል? በፍቅር ስም በወንድሞቹ እቅፍ ካልተሸሸኩ፣ በወገኖቼ ክንድ ካልተደገፍኩ፣ በትውልዱ ካልተኩራራሁ ኢትዮጵያዊነት ምን ሊፈይድ? እናም እንመለስ..ወደራሳችንና ወደቀልባችን እናዝግም::

በዘረኝነት በኩል ትውልድ ሀገር የለውም:: በእኔነት በኩል ሀገር ሰው አይኖራትም:: ሀገር እያጣን ያለነው ከኢትዮጵያዊነት ባስቀደምናቸው ምናምንቴዎቻችን ነው:: ወንድማማችነትን የተነፈግነው መሀከላችን በተበተኑ የጥላቻ ዘሮች ሳቢያ ነው:: ኢትዮጵያ ብለን ጀምረን እኛ ብለን ካላበቃን ትርፋችን እንደዚህ ቀደሙ ሞትና ጉስቁልና ነው:: እናም ስለሰላም በሰላም አብሮነታችንን እንመልስ::

ኢትዮጵያን የማዳን ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ነን:: የምንድነውም ሆነ የምናድነው ደግሞ በሀሳብ ነው:: ጠመንጃ ሀገር አያድንም:: ጦርነት ሰላም አያመጣም:: ቂም በቀል የፍቅርን ደመና ይጋርዳሉ እንጂ ፍቅር አያዘንቡም:: ጥላቻ ታሪክ ይሸነቁራል እንጂ አብሮነትን አይጥፍም:: በጦርነት ሰላም የሚመጣ ቢሆን ኖሮ በዓለም ላይ በሰላሟ ቀዳሚዋን ሀገር በፈጠርን ነበር:: ጥላቻ፣ ቂም፣ በቀል፣ ዘረኝነት፣ የታሪክ ዝንፈት፣ የትርክት ጥመት የስልጣኔ መብቀያ ቢሆኑ ኖሮ ማን በደረሰብን:: ሁሉም ግን አክሳሪዎች ናቸው..እንሆ ከስረንም ባዷችንን ነን::

እንደ ሰላም ያሉ አንዳንድ ነገሮች ያለ አጋዥና ያለደጋፊ ብቻቸውን የተፈጠሩ ናቸው:: ብቻቸውን ይፈጠሩ እንጂ ሰው የሚለውን ታላቅ ፍጡር በክብርና በልዕልና ለማኖር ከማንም የተሻሉ የመኖር ዋስትና መሆን የሚችሉ ናቸው:: በሰላም ስለ ሰላም ጽንሰ ሀሳብም የአብሮነት ምሰሶ ሆኖ ሀገር የሚያቆም ነው:: ሰላም መር በሆነ የውይይት ማዕቀፍ ውስጥ ማለፍ የነበሩትን ከመሻርና ያሉትን ሰላማዊ ከማድረግ ረገድ ይሄ ነው የማይባል ሚና አለው::

ሀገር የእኔ የአንተ የሁላችን ቀለም ናት:: የደመቀችው ተሰባጥረን፣ ተዋህደን ስለተቀየጥን ነው:: ብዙ አስተሳሰቦች፣ ብዙ አመለካከቶች፣ ብዙ ባህሎች፣ ብዙ ስርዐቶች እንዲሁም ብዙ ልማዶች ለአንድ ማህበረሰብ የቅያሜ ሳይሆኑ የትቅቅፍ አንቀልባዎች ናቸው:: ውበታችን ከእኛ እንደተፈጠረ ሁሉ የችግሮቻችን መፍትሄም ከእኛው የሚመነጩ ናቸው:: ስለሆነም በሰላም ስለሰላም እንትጋ::

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የሶማሌ ክልል ኢንቨስትመንትን ያነቃቃው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ

ኢያሱ መሰለ

ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ላለፉት ስድስት ዓመታት የሰላምን በረከት እያጣጣመ የሚገኘው የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፤ የዘመናት የልማት ቁጭቱን ለመወጣት ምቹ ሁኔታ እንደተፈጠረለት በሁሉም ዘርፍ የተሠሩት የልማት ሥራዎቹ ማሳያዎች ናቸው:: ክልሉ በግብርና ዘርፍ በተለይም የመስኖ ልማትን አዲስ የሥራ ባህሉ አድርጎት ይታያል:: በመንገድ መሰረተ ልማት ዘርፍ ያሳየው እምርታም ተስፋ ሰጭ ነው::

በክልሉ ፈጣን ለውጥ ከታየባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ የኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ነው:: ክልሉ ያገኘውን ሰላምና መረጋጋት ተከትሎ የተደረገላቸውን ጥሪ ተቀብለው በስደት ይኖሩ የነበሩ የአካባቢው ተወላጆች ወደ ሀገራቸው ተመልሰው መዋለ ንዋያቸውን በክልሉ የልማት ሥራዎች ላይ እያዋሉ ይገኛሉ::

እነዚህ የክልሉ ተወላጆች በግብርናና በትምህርት ዘርፎች እንዲሁም በሆቴሎች፣ በትምህርት ዘርፍና በፋብሪካዎች ግንባታ ብርቱ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ:: በክልሉ በተለያዩ ዘርፎች ከተከናወኑ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች መካከል በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የተከናወኑ ስራዎች ይጠቀሳሉ::

የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የክልሉን የኢንቨስትመንት አቅም በከፍተኛ ደረጃ ማነቃቃት አስችሏል፤ ኢንቨስትመንቶቹ ኢኮኖሚውን በማንቀሳቀስም የአካባቢውን ገጽታ በመቀየር እና ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል በመፍጠር አስተዋጽኦ እያበረከቱም ይገኛሉ::

በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ከለውጡ በፊት የነበሩት አጠቃላይ የፋብሪካዎች ብዛት (ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ) ከ85 አይበልጥም ነበር፤ ከለውጡ ወዲህ ግን 230 የሚሆኑ አዳዲስና ግዙፍ ፋብሪካዎች መገንባታቸውን ከክልሉ ርእሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሃመድ ቃለ ምልልስ ባደረግንበት ወቅት አረጋግጠውልናል::

በስራ ላይ ከሚገኙ ፋሪካዎች መካከል ከፍተኛ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስበትና ለክልሉ እና ለሀገር አለኝታ የሆነው ‹‹ሱዌይስ ሞተርስ ኩባንያ›› (Suweys Motors Company) አንዱ ነው:: ኩባንያው በጂግጂጋ ከተማ የሚገኝ ሲሆን፣ ‹‹ጄቱር›› እና ‹‹ሱዙኪ›› ዲዛየር መኪኖችን እየገጣጠመ ለሀገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል::

ይህ ለግንባታው ብቻ 250 ሚሊዮን ብር ኢንቨስት የተደረገበት ፋብሪካ የሚገጣጠሙ የመኪና አካላትን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትም እንዲሁ ከፍተኛ ካፒታል ያንቀሳቅሳል::

የሱዌስ ሞተር ኩባንያ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዲ ኢብራሂም እንዳሉት፤ ፋብሪካው በቀን አምስት መኪኖችን እየገጣጠመ ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ጀምሯል:: ሥራ በጀመረ በአንድ ወር ቆይታውም፣ በሁለት ሳምንት ውስጥ ብቻ 40 ጄቱር እና 12 ሱዙኪ ዲዛየር መኪኖችን ገጣጥሞ ለገበያ በማቅረብ ሸጧል::

ከፍተኛ የግዢ ፍላጎት እንዳለ የተናገሩት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፣ ቅድመ ክፍያ ፈጽመው ለመግዛት ወረፋ የያዙ በርካታ ሰዎች ስለመኖራቸውም አስታውቀዋል:: ኩባንያው የሀገር ውስጥ የመኪና አቅርቦት ፍላጎትን ማሟላት ብቻ ሳይሆን መኪኖችን ወደ ጎረቤት ሀገራት የመላክም ራዕይን ይዞ እየሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ፋብሪካው ስራ በጀመረ አጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ ለሦስት መቶ ሰዎች ቋሚ የሥራ እድል መፍጠሩን የተናገሩት አቶ አብዲ፣ ኩባንያው ወደፊት የማስፋፊያ ስራ ሲያካሂድና የንግድ ሰንሰለቱን ሲያረዝም ለሌሎች በርካታ ዜጎችም የሥራ እድል እንደሚፈጥር ተናግረዋል::

‹‹ሳሂድ ሜታል ኢንዱስትሪ ኢንጂነሪንግ›› ሌላው በጂግጂጋ ከተማ የሚገኝ የከባድ መኪኖች አካላት ማምረቻ እና መገጣጠሚያ ግዙፍ ኩባንያ ነው። የኩባንያው የገበያ ክፍል ኃላፊ አቶ ነስር





ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ



ያሲን እንደሚሉት፤ ኩባንያው በራሱ ቅርጽ ማውጫ ማሽኖች ተጠቅሞ የከባድ መኪኖችን አካላት፣ ቦቴና የነዳጅ ማደያ ታንከሮችን ያመርታል። ሞተር እና ጋቢና ብቻ ያላቸውን ከባድ የጭነት መኪኖች ከውጭ እያስገባ የቀረውን አካላቸውን በፋብሪካው ውስጥ ሰርቶና ገጣጥሞ ተሽከርካሪዎቹን ሙሉ እያደረገ ለገበያ ያቀርባል ሲሉም ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኩባንያው ለ270 ሰዎች የሥራ እድል ፈጥሯል። በኩባንያው ውስጥ ከምንም ተነስተው ሥራ የጀመሩ ሠራተኞች ዛሬ ሙያ አካብተው ከፍተኛ ተከፋይ እስከመሆንም ደርሰዋል።

በክልሉ ከጂግጂጋ ቀጥሎ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ያሉባት የክልሉ ሲቲ ዞን ዋና ከተማ ሺኒሌ ነች:: ሺኒሌ በኢትዮ-ጂቡቲ አውራ መንገድ ላይ የምትገኝ እንደመሆኗ የውጪና ገቢ ንግዱን ከማሳለጥ አንጻር የራሷን አስተዋጽኦ የምታበረክት የኢኮኖሚ ኮሪደር ስትሆን፣ ለኢንቨስትመንትም ምቹ ከሚባሉ የሀገራችን ከተሞች ትመደባለች:: በዚህም ምክንያት ምርቶቻቸውን ወደ ሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እና ወደ ውጭ ሀገር የሚያሰራጩ ፋብሪካዎች ተገንብተውባታል::

የሸኒሌ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ኢብራሂም ሮብሊ በበኩላቸው እንደሚገልፁት፤ በሸኒሌ ወረዳ በተለይም በሸኒሌ ከተማ የቶኔ እና የመርማርሳ ቀበሌዎች የኢንዱስትሪ መንደር ተብለው ተለይተዋል:: ለኢንዱስትሪዎች ቁጥር እየጨመረ መምጣት የአካባቢው ሰላም መሆን አስተዋጽኦ አበርክተዋል::

ፋብሪካዎቹ ከግንባታ ጊዜያቸው ጀምሮ ወደ ስራ እስከገቡበት ጊዜ ድረስ ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል እየፈጠሩ ስለመሆናቸውም ጠቅሰዋል። በርካታ የአካባቢው ተወላጆችና ከሌላ አካባቢ የመጡ ዜጎችም ጭምር በፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው እየሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል:: የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች በዞኑ መኖራቸውን ጠቅሰው፣ የግራናይትና ማርብል ፋብሪካው በተለይ በድሬዳዋና በአካባቢው ቤት ለሚገነቡ ሁሉ ጥሩ አድል ይዞ መምጣቱን ገልጸዋል::

በተጨማሪም ከ10 ሺ እስከ 25 ሺ ሊትር ውሃ መያዝ የሚችሉ ሮቶዎችን፣ የስፖንጅ ፍራሽ፣ የቆርቆሮ፣ የሳሙና እና የመጠጥ ውሃ ማምረቻ ፋብሪካዎች እንዳሉም አብራርተዋል::

ወረዳው የገቢ ወጪ ንግድ የሚተላለፍበት መሆኑን ጠቁመው፣ ይህም በኢንቨስትመንት መስኮች ለተሰማሩ ባለሀብቶች አመቺ እንደሆነ አስታውቀዋል:: ይህን ሁሉ ታሳቢ በማድረግም ባለሃብቶች እየመጡ በተለያዩ ሥራዎች እንዲሰማሩም ጥሪ አቅርበዋል::

በተለይም በሪልስቴትና አምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 125 ሄክታር መሬት ዝግጁ መደረጉንም ጠቁመዋል:: የውሃና የመብራት መሰረተ ልማት ዝግጁ በማድረግና ቀልጣፋ መስተንግዶ ለመስጠት ተዘጋጅቶ አልሚዎችን እየጠበቀ መሆኑንም አስታወቀዋል::

ከሸኒሌ-ድሬዳዋ እየተገነባ ያለው አዲስ የአስፋልት መንገድም በከተማዋ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር አመልክተው፣ ለአካባቢው የንግድ እንቅስቃሴም ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥር አስረድተዋል::

የወረዳው የኢንቨስትመንት ቢሮ የሚመራው በክልሉ ምክትል ርእሰ መስተዳደር እንደሆነ ጠቁመዋል:: የአካባቢው ጸጥታና ሰላም አስተማማኝ እንደሆነ ጠቅሰው፣ ባለሃብቶች ወደ አካባቢው በመምጣት በልማቱ እንዲሰማሩ ጥሪ አቅርበዋል::

በሸኒሌ ከተማ ከተገነቡት ግዙፍ ፋብሪካዎች መካከል አንዱ ‹‹ኢፎፒክ ፎምና ፕላስቲክ ፋብሪካ›› አንዱ ነው:: የኩባንያው የፕሮዳክሽን ማናጀር አቶ ሙአዝ ብርሃኑ ኩባንያው ሮቶ፣ የፕላቲክ ቱቦችን፣ ወንበሮችን እና የስፖንጅ ፍራሾችን ያመርታል ይላሉ::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ፋብሪካው ሥራ ከጀመረ አምስት ዓመቱ ነው:: እስከ 600 ሚሊዮን ብር ካፒታል ወጪ ተደርጎበት የተቋቋመ ነው:: ከ500 እስከ 10 ሺህ ሊትር መያዝ የሚችሉ የተለያየ መጠን ያላቸውን ከ25 እስከ 30 የሚደርሱ ሮቶዎች በቀን ማምረት ይችላል::

እስካሁን እየሰራ የሚገኘው በአንድ ፈረቃ ቢቻ ሲሆን፣ ለ150 ሰዎችም የሥራ እድል ፈጥሯል:: 24 ሰዓት መስራት ሲጀምር የሰራተኞቹን ቁጥር በሶስት እጥፍ በማሳደግ ለ450 ዜጎች የስራ እድል የመፍጠር አቅም ይኖረዋል:: የፕላስቲክ ምርቶቹን ከሀገር ውስጥ ገበያ በተጨማሪ እንደ ጂቡቲና ሶማሌላንድ ለመሳሰሉ ሀገራትም ተደራሽ ያደርጋል::

በዚያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኘው የስፖንጅ ፋብሪካም በቀን (በስምንት ሰዓት ውስጥ) እስከ አምስት ሺህ የተለያየ መጠን ያላቸው ፍራሾችን ያመርታል:: ምርቱ ሙሉ ለሙሉ ለሀገር ውስጥ ገበያ በተለይም ለምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ እንደሚቀርብ የተናገሩት አቶ ሙዓዝ፣ የገበያው ውስንነት ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ እንዳያመርት ተግዳሮት ስለመሆኑም ጠቅሰዋል::

ለፋብሪካው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን ከውጭ ሀገራት እንደሚያስገቡ የተናገሩት ማናጀሩ፣ ሸኒሌ ለጂቡቲ ወደብ ቅርብ መሆኗ ግብዓት ለማቅረብና ምርቱን ወደ ውጭ ለመላክም አመቺ እንደሆነች ገልጸዋል::

ከውጭ የሚመጡ ግብአቶችን ለማስገባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት በስራቸው ላይ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑንም ማናጀሩ ጠቅሰዋል:: በውጭ ምንዛሪ እጥረት የተሟላ ግብዓት ማቅረብ አለመቻሉን አስታውቀው፣ በእነዚህ ችግሮች ሳቢያ ፋብሪካው አንዳንድ ጊዜ ለመቆም እንደሚገደድም ተናግረዋል::

ሌላው በሸኒሌ ወረዳ በኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩት የ‹‹ዋቢ ግሩፕ ማርብል እና ግራናይት ፋብሪካ›› ባለቤት አቶ ጣሂር አብዲ ናቸው:: መንግስት ባለሃብቶች ወደ ሀገራቸው ገብተው በልማት ሥራ እንዲሳተፉ ያስተላላፈው ጥሪ እና የሚያደርገው እገዛ እንዲሁም በክልሉ የተገኘው ሰላም ከሚኖሩበት የስደት ሕይወት ወደ ሀገራቸው ገብተው በልማት ሥራ ላይ እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረላቸው አስታውቀዋል::

እርሳቸውና መሰል ጓደኞቻቸው በአክሲዮን ተደራጅተው በአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ‹‹ዋቢ ግሩፕ ማርብል እና ግራናይት ፋብሪካ››ን ማቋቋማቸውን ገልጸዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ፋብሪካው ግንባታው ተጠናቆ ወደ ማምረት ስራ ለመግባት እየተዘጋጀ ይገኛል:: ለሕንጻ ቤቶች ንጣፍ የሚሆኑ የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን ምርቶች ከድንጋይ እና እምነበረድ በማምረት የሀገር ውስጥ ፍላጎትን የማሟላትና ከውጪ የሚገቡ መሰል ምርቶች የመተካት፤ ምርቱን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ራዕይም አለው:: ለፋብሪካው ግብዓት የሚውሉና በአካባቢው የሚገኙ ግብአቶችን ወደ ፋብሪካው እያስገባም ይገኛል::

በስራ እድል ፈጠራ በኩልም በፋብሪካው ተከላ ሂደት ከአንድ መቶ በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የስራ እድል መፍጠሩን ገልጸው፣ በሙሉ አቅሙ ሥራ ሲጀምር ደግሞ በሶስት ፈረቃ በሚከናወነው ሥራ ለበርካታ ሰዎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጠር ተናግረዋል::

አቶ ጣሂር፤ ፋብሪካው በቅርቡ ሥራ እንደሚጀምር ጠቅሰው፤ አሁን የሚስተዋለው የመብራት መቆራረጥ የሚቀጥል ከሆነ የማምረቱን ስራ እንደሚጎዳው ተናግረዋል:: የመብራት መቆራረጡ ጉዳይ ከወዲሁ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ትኩረት እንዲሰጠው ጠይቀዋል::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# የሚያዋጣን ከሰላም ጎን መቆም ነው

**ፍሬው ማንችሎት**

ወቅቱ የክረምት መግቢያ የሰኔ ወር ቢሆንም የበጋዋ ጸሃይ ቦታዋን ለመልቀቅ የተናነቃት ይመስል ከዝናቡ ጋር ግብግብ ገጥማለች:: በየሰዓቱ ብልጭ እያለ ልብ የሚያቀልጠው የደመና ግላጭ የአላፊ አግዳሚውን አናት ያነደው ይዟል::

ወደ ማምሻ ግሮ ሰሪ እያዘገመ የነበረው ተሰማ አናቱ በጸሃይ ግሎ ብስጭት ብስጭት ብሎታል:: ቀዝቀዝ ማለት በመፈለጉ ብቻ ሳይሆን ወዳጆቹንም ፈልጎ ማምሻ ግሮ ሰሪ ተሰየመ::

ተሰማ ተቀምጦ እግሩ መሬት ነክቶ በደንብ ካረፈ በኋላ፤ የሚጠጣውንም አጣጥሞ የእጅ ስልኩን መነካካት ጀመረ:: ጊዜው ባለመምሸቱ ጓደኞቹ ተሰማ መንግስቴ እና ገብረየስ ገብረማሪያም ገና ወደ ማምሻ ቤት አልመጡም ነበር:: እስከዛው አይኑን ወደ ቴሌቪዥኑ ሲወረውር በአማራ ክልል ሰላም ለማውረድ ጥረቶች መጀመራቸውን እና የሰላም ካውንስል መቋቋሙን አዳመጠ:: ደስ አለው::

ብዙም ሳይቆዩ ዘውዴ እና ገብረየስ እንደልማዳቸው አምሽተው ሳይሆን በጊዜ ወደ ማምሻ ግሮሰሪ ብቅ አሉ:: ዘውዴ በፈገግታ ተቀበላቸው:: ዘውዴ ለተሰማ ‹‹የተፈፀመውን ሰማህ አለው?›› ገብረየስ ቀደም ብሎ ‹‹ አልሰማም፤›› ሲል ምላሽ ሰጠ:: ተሰማ ግራ ገባው ‹‹ የተፈፀመው ምንድን ነው? መቼም ይሔ በየማህበራዊ ድረገፁ የሚለጠፈውን ውሸት ይዛችሁ እንዳይሆን፤ የሆነው ምንድን ነው ምላሽ ስጡኝ::›› አለ::

ተሰማ ‹‹ አማራ ክልል ሰላም ሊወርድ ነው:: የሰላም ካውንስል ሊቋቋም መሆኑን በሚዲያ ሰማሁ ብሎ ››ደስታውን አበሰራቸው:: እነሱም ደስታው ተጋባባቸው:: በተለይም ተሰማ አማራ ክልል በነበረው ግጭት ምክንያት ከዘመዶቹ ጋር ከተገናኘ ረጅም ጊዜው ነበር:: የደህንነታቸው ጉዳይ አብዝቶ ያሳስበው ስለነበር እነሱም ሁልጊዜ አብረው ይጨነቁ ነበር:: እናም በሁሉም ፊት ላይ የተስፋ ብርሃን ይነበብ ነበር::

ተሰማ የጓደኞቹን መደሰት ካየ በኋላ ወጉን ቀጠለ:: ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ ዳር ድንበር የሚዋደቅ፤ ከራሱ በፊት ሀገሩን የሚያስቀድም፤ ቀኝ ገዢዎችንና ሌሎች ወራሪ ኃይላትን አሳፍሮ የሚመልስ ጀግና ሕዝብ ነው:: ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ሀገራት ነጻነትና እኩልነት የሚታገሉ፤ በአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት የሆኑ ኩሩ ሕዝቦች ናቸው:: ይህም ጀግንነትና አይበገሬነት በተባበሩት መንግስታት ጭምር እውቅና አግኝቶ ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን በሩዋንዳ፤ በቡርንዲ፤ በላይቤሪያና በሶማሊያ ተሰማርቶ ጀግንነቱን አስመስክሯል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀግንነቱን ያህል ሰላም ወዳድም ነው:: በየትም ሥፍራ ቢኖር፣ የትኛውንም እምነት ቢከተል፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ቢገለገል፣ ባህሎቹና ልማዶቹ ቢለያዩም ለሰላምና አብሮነት ሰፊ ቦታን ይሰጣል:: ሰላም የእሴቶቹ አንዱ መገለጫ ነው::

ሆኖም ከዚህ የኢትዮጵያውያን ባህል ባፈነገጠ መልኩ ፍላጎታቸውን በነፍጥ ማሳካት የሚፈልጉ ቡድኖች እየተበራከቱ መጥተዋል:: ከውይይት ይልቅ ነፍጥ ማንሳት የሚቀናቸውና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ የሚረብሹ፤ አብሮነቱን የሚያውኩ፤ የኢትዮጵያን መረጋጋትና ሉአላዊነት የሚገዳደሩ ቡድኖች እዚህም እዚያም አቆጥቁጠዋል::

እነዚህ ወገኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ብጥብጥም ልማት ተደናቅፏል፤ የሰዎች ወጥቶ መግባት ተስተጓጉሏል፤ አለፍ ሲልም የሀገር ህልውናንም አደጋ ላይ ወድቋል:: እኛም ባለፉት ግዝያት የተጎዳነው እና ለብዙ ሃሳብ የተዳረግነው በእነዚህ ቡድኖች የተነሳ ነው::›› በማለት ሃሳቡን አሳረገ::

ዘውዴ ቀበል አደረገና ጨዋታውን ቀጠለ:: ‹‹ዘውዴ ልክ ነህ:: ባለፉት ግዚያት ምን ያህል እንደተጨነቅክ እናውቃለን:: ከአንተ አልፎ እኛም ስንጨነቅ ቆይተናል:: አየህ ኢትዮጵያ ውስጥ የአንዱ ሰላም ደፍርሶ የሌላው ሰላም ሊረጋገጥ አይችልም:: አንዱ ጥይት እየጮኸበት አንዱ የሰላም አየር ሊተነፍስ አይችልም:: እጣችን የተሳሰረ ነው:: ስለዚህም አብረን ችግሮቻችንን መፍታትና በሰላም መኖር አለብን::

አሁን እኛ የተቸገርነው ሕዝብ ሳይሾማቸው ለሕዝብ ቆመናል በሚሉ ቡድኖች ነው:: እነዚህ ቡድኖች ሕዝብ ሳይሾማቸው የሕዝብ ወኪል ነን ከማለታቸው በሻገር አሉ የሚሏቸውን ችግሮች እንኳን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አይፈልጉም::

እነዚህ ቡድኖች ችግርን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ነውጠኛ ደጋፊዎችን የማሰባሰብ ሴራ ውስጥ ስለሚገቡ፣ በኢትዮጵያ እዚህም እዚያም ግጭቶች በርክተው ይታያሉ:: እነዚሁ ኃይላት ኃላፊነት የጎደላቸው ስለሆኑም ግጭትና መገዳደልን ጨምሮ የአገርን ተስፋ የሚያጨልሙ ድርጊቶች እንዲበራከቱ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

ለአገርና ለሕዝብ ከማሰብ ይልቅ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ስለተጠናወታቸውም ቆመንለታል ያሉትን ሕዝብ ሳይቀር በቁሙ ሲዘርፉ ተስተውለዋል::

እነዚህ ቡድኖች ከመተማመን ይልቅ ጥርጣሬ፣ ከትብብር ይልቅ መገፋፋት፣ በግልጽ ከመነጋገር ይልቅ መተማማት ስለሚቀናቸው የማህበራዊ ሚዲያዎች እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሕዝቡን አላስፈላጊ ወደ ሆነ ጥርጣሬ ውስጥ በመክተት አንዴ በብሔር ሌላ ጊዜ በሃይማኖት እየከፋፈሉ የዘመናት አብሮነቱን ሊነጥቁት ሲሯሯጡ ይታያሉ:: በእነዚህ ስግብግቦች የተነሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከባድ ጊዜን ለማሳለፍ ተገዷል:: ጓደኛችን ተሰማም የነዚሁ ቡድኖች አንዱ ሰለባ ነው:: ከእሱም አልፎ እኛም ተጎጂዎች ሆነናል::››ሲል ሃሳቡን አሳረገ::

የሁለቱንም ሃሳብ በአንክሮ ሲያዳምጥ የቆየው ገብረየስ ድመጹን ስሎ ወደ ውይይቱ ተቀላቀለ:: ‹‹ያላችሁት ምንም የሚወድቅ ነገር የለውም:: እንደውም እስካሁን ዝምታን መምረጣችን ለችግሩ መባባስ አጋዥ ሆነን ቆይተናል የሚል እምነት አለኝ::

እነዚህ ቡድኖችና ደጋፊዎቻቸው በሚለቋቸው መረጃዎች ጭምር ተወናብደን በተዘዋዋሪ ከሰላም ጎን መቆም አቅቶን ቆይተናል:: እነዚህን ቡድኖች ድርጊታቸው የሚያስቆማቸው የጸጥታ ኃይል ሲመጣ ደግሞ ግበረ አበሮቻቸውን ሰብስበው በሰፊው ስም የማጥፋት ዘመቻ ውስጥ ይገባሉ::

የኢትዮጵያን ሰንደቅ ለብሶ ታላላቅ ድሎችን የተጎናፀፈውን ጀግና የመከላከያ ሰራዊታችንንም በማጠልሸትም ኢትዮጵያን ለማሳነስም በቀቢጸ ተስፋ ሲሯሯጡ ታይተዋል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ እጅግ በጣም ሰላማዊና ለሕግ ትልቅ ትኩረት ስለሚሰጥ ለአመፅና ለብጥብጥ ሥፍራ የለውም እንጂ የእነዚህ አካላት ድርጊት ሀገርን የማፍረስ ዓላማ ጭምር ያለው ነው::

ስለዚህም አሁን ሁላችንም የሚያዋጣን ከሰላም ጎን መቆም ነው:: መወቃቀስና አንዱ አንዱ ላይ ጣት መጠቆሙ ያመጣልን ፋይዳ የለም:: የሰላም ሃሳብ የሚያነሳን ወገን ሁሉ መደገፍ አለብን:: ተሰማ እንዳለው በአማራ ክልል ያለው ግጭት ማብቃት አለበት:: ሰዎች በሰላም ወጥተው የመግባት ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ሊከበር ይገባል:: እንደተባለውም የሰላም ካውንስል መቋቋሙ አንድ እርምጃ ነው ብዬ አምናለሁ ››ብሎ ሃሳቡን ቋጨ::

ተሰማ ሃሳቡን መደገፋቸው አበረታታውና ቀጣይ ሃሳብ ለማንሳት ተዘጋጀ:: ‹‹ እንደ አንድ ዜጋ ሁላችንም በየአቅማችን ኢትዮጵያን ማትረፍ ግዴታችን ነው፤ የሚል እምነት አለኝ:: ኢትዮጵያን ለማትረፍ በሚሠራው ሥራ ሰዎች ሊጎዱ ይችላሉ:: ያንን ተከትሎ ቅሬታ፣ አለፍ ሲል ቁጣ አልፎ ተርፎ ተቃውሞ እና አመፅ ሊያጋጥም ይችላል:: ይህ የሚጠበቅ ነው::

በተጨማሪ የሰው ፍፁም የለውም፤ በዚህ ሂደት ውስጥ መፈፀም የሌለባቸው ድርጊቶች ተፈፅመው ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ምንም ሆነ ምን ከማንም ሰው በላይ ኢትዮጵያ ትልቃለች:: ኢትዮጵያ የብዙዎች ደም የፈሰሰላት፤ ብዙዎች የተሰውላት አገር ናት:: ስለአገራችን ስናስብ እና ስንጨነቅ አገራችንን ለማትረፍ የምንሰራውን ሥራ ተከትሎ ጉዳዩን ባለመረዳት ወይም ከግል ጥቅም ጋር በማገናኘት የሚቃወም ሰው ቁጥር እያደገ ሊመጣ ይችላል፤ ሆኖም ዋነኛው ጉዳያችን ኢትዮጵያ ናትና በቅድሚያ ሀገራችንን ልናተርፍ ይገባል::

በዋነኝነት ደግሞ ኢትዮጵያን ማትረፍ የምንችለው ሰላሟን በማስጠበቅ ነው:: በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሁላችንም ወደ ብሄራችን ወይንም ወደ ኃይማኖታችን በማድላት ኢትዮጵያን ጎድተናት ይሆናል:: ሆኖም የምንከስበት አሁን ነው ብዬ አስባለሁ:: ስለዚህም ሁላችንም ኢትዮጵያን ለመካስ ምን ያህል ተዘጋጅተናል::

እስኪ ወደ እራሳችን እንመልከት እኔ፤ አንተ፤ እናንተ አገራችሁን ኢትዮጵያን ብላችሁ አስባችሁ ትሠራላችሁ?›› ሲል ዘውዴን ጠየቀው:: ዘውዴ በበኩሉ ‹‹ ችግሩ አገራችንን አስበን ቀንና ለሊት ተግተን ብንሠራም፤ ከውስጥም ከውጪም ጠላት በዛብን:: ውጪ ያለው ጠላት ኢትዮጵያን ብሎ ስለ ኢትዮጵያ የሚሠራውን ማጥፋት ይፈልጋል:: ምክንያቱም ኢትዮጵያን የማፍረስ እና ታሪኳን የማጥፋት ፍላጎት አለው:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ላይ በተለያየ መንገድ ዘመቻ ላይ ነው:: ይህ ስውር የውጪ የጠላት ኃይል ጠላትን የሚቃወመውን ሁሉ መደገፍ እንዳለበት አምኖ የውጪ ጠላት ከአገር ውስጥ ጠላት ጋር በመተባበር እየሠራ ነው:: የውስጥ ጠላት እንዴት ተፈጠረ? ካላችሁ በአሠራር ስህተት የተፈጠሩ ጥቃቅን ጉዳዮችን በማጉላት እና ያንንም በማስተጋባት ሰዎች ስለአገር የሚያስቡትን፣ ስለአገር የሚሰሩትን የሚጠሉበት ሁኔታ በመፈጠሩ ነው:: በሌላም በኩል ለውጭ ጠላቶች የሚላላኩና ምንዳ የሚጣልላቸውም ቀላል አይደሉም::

በየጊዜው በሚፈጠሩ ወቅታዊ ሁኔታዎች በመሳብ ዋናውን ሀገር ጉዳይ የሚረሱ ቀላል ቁጥር የላቸውም:: ሀገር ግንባታ ደግሞ አልጋ በአልጋ አይደለም፤ በአንድ ጀንበር ተጀምሮ በአንድ ጀንበር የሚያበቃም አይደለም:: ብዙዎች የተማሩ የተባሉ ሰዎች ሳይቀሩ አይተው መረዳት ተስኗቸዋል:: መደገፍ ያለባቸውን ከመደገፍ ይልቅ ዘላለማቸውን የጦርነት ነጋሪት በመጎሰም አሁንም አገር ለማጥፋት እየተባበሩ ነው::

የአተያይ እና የአመለካከት ልዩነት የተለመደ ነው:: ስለአገራችን ስናስብ የችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ ሁከትና ብጥብጥ ነው ብሎ ማሰብ አይገባም:: በመነጋገር እንጂ በኃይል እርምጃ የትም መድረስ አይቻልም:: ተነጋግሮ ችግሩን ከስር መሰረቱ መፍታት ካልተቻለ በሁከትና ብጥብጥ የሰው ሕይወት ይጠፋል፤ የሀገር ሃብት ይወድማል::

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹ ታዲያ የኃይል እርምጃ እንዳይወሰድ አንዱ የገዛ ሌላኛውን ወንድሙን እንዳይወጋ ከተፈለገ ሰላም እና ሥርዓት መስፈን አለበት:: ዋነኛው ማንም ስለኢትዮጵያ ቀን እና ለሊት የሚያስበው ሰው መነሻ እና መድረሻው የኢትዮጵያ ሰላም እና ዕድገት ብቻ ነው:: ያለሰላም ዕድገት ዘላቂ መሆን አይችልም::›› ሲል ተናገረ::

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር እጅግ በጣም የተወሳሰበ ነው:: ብዙዎቻችን አንዳንዴም የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ሳይቀሩ ስላለው ችግር ለሕዝቡ የማሳወቅ ክፍተት አለባቸው:: መረጃ በወቅቱ ለሕዝብ ከማድረስ አንጻር ክፍተት አለ:: ሕዝቡ በአግባቡ መረጃ ቢደርሰው መንግስትን በአግባቡ መረዳት ይችላል፤ ከመንግስት ጋር ሆኖም የተጀመረውን ሀገርን የማቅናት ዘመቻ ከግቡ ማድረስ አይሳነውም::›› ሲል ያለውን እምነት ገለፀ::

ተሰማ በበኩሉ ‹‹ ዋነኛው ችግር አብዛኞቻችን የሩቅ ተመልካችና ተቺ ሆነን መገኘታችን ነው:: አለፍ ሲልም በሽርፍራፊ ሳንቲም ሀገራችንን የመንቀይር መብዛታችን ነው:: ያለንን ገንዘብ እንኳን መብላት የምንችለው ሀገር ስትኖር መሆኑን ዘንግተናል:: ማንም የማይክደው ብዙ ሰው ስለአገር ይጨነቃል:: ምክንያቱም ሕይወቱ ከአገሩ ጋር የተቆራኘ ነው:: ነገር ግን ጥቂቶች በሚፈጥሩት ውዥንብርና ትርምስ የብዙሃኑ ሕይወት መታመሱ የሚያሳዝን ነው::

ሰውን ከምንም በላይ ተግባር ያሳምነዋል፤ ማየት ማመን ነው:: ሰው መልካም ነገር ሲያይ ይደሰታል፤ ያመሰግናል:: ስህተቶች ሲኖሩም አግባብ በሆነ መልኩ ማስረዳት ይገባል:: እጸጽ እየፈገሉ ሰዎችን ለአመጽ መጥራት እና አላስፈጊ ሁከት መፍጠር ትርፉ ኪሳራ ብቻ ነው:: በእርግጥ አንዳንድ ሰዎች ከአመጽ ትርፍን፤ ከሀገር ኪሳራ ሃብትን የሚጋብሱ አሉ:: እነዚህ ሰዎችን መምከር በክንቱ መድከም ነው:: ምክንቱም እነዚህ ሰዎች ገቢ በሁከትና ብጥብጥ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ሰላም ወረደ ማለት እነዚህ ሰዎች ሃብት ነጠፈ እንደማለት ነው:: ስለዚህም ሁላችንም ልንነቃ ይገባል:: ለጥቂቶች ብለን እራሳችንን መስዋዕት ማድረግ የለብንም:: ሁላችንም በደስታ መኖር የምንችለው ሀገር በሰላም ውላ ስታድር መሆኑን መገንዘብ አለብን:: ›› ብሎ በረጅሙ ተንፍሶ ሃሳቡን አሳረገ::

**ኢትዮጵያ ውስጥ የአንዱ ሰላም ደፍርሶ የሌላው ሰላም ሊረጋገጥ አይችልም:: አንዱ ጥይት እየጮኸበት አንዱ የሰላም አየር ሊተነፍስ አይችልም:: እጣችን የተሳሰረ ነው:: ስለዚህም አብረን ችግሮቻችንን መፍታትና በሰላም መኖር አለብን::**

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## ዶሳይስ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

"ዶሳይስ" ከደራሲና ገጣሚ ኩሪ አየለ ኃይሌ ከሰሞኑ ለአንባቢያን የቀረበ ምርጥ የመጽሐፍ ጦማር ነው። ከዚህ ቀደም የግጥም መድብሏን ጨምሮ ሁለት መጻሕፍትን ያበረከተችልን ደራሲዋ ለሦስተኛው በዶሳይስ መጥታለች።

የአሁኑ ዶሳይስ መጽሐፏ በአጫጭር ልቦለዶች ታሪክ ተሰባጥሮ የቀረበ ባለ ብዙ የሀሳብ ጅማት ነው። ማኅበራዊ ማኅብረሰብ፣ ሀገራዊ ሀገርና ሕዝብን ጨብጦ የያዘ የንቃት መንገድና መንገደኛም ነው። በማኅበረሰባችን ውስጥ ያሉትን ህጸጾች በተለያዩ መንገዶች እየነቀሰ የመመለሻውን ፍኖት ያንጸባርቃል። ምናልባትም የደራሲዋን ውስጣዊ ስብዕናና የአመለካከት ጮራዎቿን የሚፈነጥቅም ዓይነት ነው። በቅርቧ ሆኖ የሚያውቃት አንድ አንባቢ ምናልባትም ከእርሷ ጋር እያወጋ ያለ ያህል መስሎ ሊሰማው ይችላል። የምረቃ ስነ ስርዓቱ ቅዳሜ ሰኔ 22 ቀን 2016 በብሔራዊ የቲያትር አዳራሽ ውስጥ በጉምቱ የጥበብ ባለሙያዎችም ተመርቋል።

ወደ መጽሐፉ ከማቅናታችን በፊት በመጀመሪያ ግን ደራሲዋ ማን ናት?

ደራሲና ገጣሚ ኩሪ አየለ ሀይሌ በአዲስ አበባ ተወልዳና አድጋ በወይዘሮ ቀለመወርቅ፤ ቀጥሎም በየካቲት 12 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቃለች። የመጀመሪያ ዲግሪዋንም በአማርኛ 'ፎክሎር'፤ እንዲሁም የሁለተኛ ዲግሪዋን 'በዲፕሎማሲ ኤንድ ኢንተርናሽናል ሪሌሽን' ተቀብላለች። ሁሌም በመልካም ሥነ ምግባር ትውልዱን የመገንባት ሥራዎችን ሥትሰራ ኖራለች። በመምህርነት ሙያም አገልግላለች። አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር ውስጥ የግንኙነት ዘርፍ ዳይሬክተር ሆና በመሥራት ላይ ትገኛለች። ደራሲዋ ለሥነጽሁፉ ላደረባት የተለየ ፍቅር መሠረቱ መላው ቤተሰቡ እንደሆነ ትናገራለች። በተለየ ሁኔታ ደግሞ አባቷን ትጠቅሳለች።

አባቷ መምህር አየለ ኃይሌ በደርግ መንግሥት በነበረው የመሠረተ ትምህርት የዘመቻ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የነበራቸው ሰው ናቸው።

በወቅቱም ማኅበረሰቡን በማስተማርና በሚያከናውኗቸው ሥነጽሁፋዊ እንቅስቃሴም ይታወቃሉ። ከማስተማሩ ጎን ለጎንም በግጥሞቻቸው ወኔ ሲቀሰቅሱም ነበር።

"የአባቶቼ ወኔ ተቀሰቀሰብኝ፤
የእናቶቼ ወኔ ተቀሰቀሰብኝ፤
መሀይምነትን ግጨው ግጨው አለኝ።"

ይህ ግጥማቸውም በማኅበረሰቡ ውስጥ ሰርጾ በመግባቱና በጣም በመታወቁ በሰፈሩ ውስጥ ልጆቻቸው "የግጨው ግጨው ልጆች" ተብለው ይጠሩ እንደነበረም በደራሲዋ የህይወት ማኅደር ውስጥ ተቀምጧል።

ደራሲና ገጣሚ ኩሪ አየለ ኃይሌ ዶሳይስን ጨምሮ አንድ የግጥምና ሌላ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ፤ በአጠቃላይ ሦስት መጻሕፍትን ለህትመት ብርሃን አብቅታለች። እነዚህ ለመታተም የበቁ እንጂ በህይወት ደረጃ እስከዛሬ ድረስ በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች የሰነቻቸው የጥበብ ሥራዎቿ እልፍ ናቸው። ለአብነትም በ1990ዎቹ አጋማሽ "ወንደላጤዎቹ" የተሰኘ ተከታታይ የግጥም ሥራዋን ረዘም ላለ ጊዜ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ስታቀርብ ቆይታለች። "የዓባይ ዘመን ብዕር" በሚል ርዕስ በዓባይ ግድብ ዙሪያ የተጻፉ ግጥሞች ስብስብ እትም ውስጥም "ዓባይ ትዳር ሆነ" የሚለው የግጥም ሥራዋ ተካቶላታል።

አሁን ደግሞ "ዶሳይስ" ብላናለች። ገና ርዕሱን ስንመለከትም ሆነ ስንሰማ መቼም ስለ ትርጓሜው መጠየቃችን አይቀርም። "ዶሳይስ" ምንድነው? ከየትስ መጣ? ... የቃሉ ሀረግ የተመዘዘው ከወላይትኛ ቋንቋ ውስጥ ሲሆን ትርጓሜውም "እወዳችኋለሁ!" እንደማለት ነው። ትልቅና ደስ የሚል ፍቅር መግለጫ ፅንሰ ሀሳብ ነው። ለማንስ? ... ስለምኑ? ካላችሁ ምላሹን መጽሐፉ ራሱ ይነግራችኋል።

በዶሳይስ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ውስጥ ተካትተው የሚገኙት ይዘትና ጭብጦች በርከት ያሉ ናቸው። አብዛኛዎቹም የማኅበረሰቡን ባህላዊ እሴትና ወግ አሁን ባለውና በሚመጣው ትውልድ ውስጥ ለማስረጽ የሚቃትቱ ናቸው። ደራሲዋ ጥንት የለመድናቸውን ማኅበረሰባዊ መስተጋብሮቻችንን ከፍ ባለደረጃ አጉልቶ ለማሳየት የተጨነቀችበት ይመስላል። ዘመድ ከዘመዱ፣ ጎረቤት ከጎረቤቱ፣ ወዳጅም ከወዳጁ ጋር ተሰባስቦ በጋራ የፍቅር ጨዋታ ሲያነሆልሉ በማሳየት ከጥንቱ፤ ከረሳነው ላይ እንድንመለስበት ጥሪ ታጣጥረናለች። በዕድርና በዕቁቡ፣ በደስታና በሀዘኑ ሁሉ አንዱ ከአንዱ ጋር የሚቆምበትን የማኅበራዊ ህይወት መደላድሎቻችንን በመከፈት ከገጸ ባህሪያቱ ውስጥ ቁልጭ አድርጎ ዶሳይስ ያስመለክተናል። በበዓላቱ ሁሉ እስላም ክርስቲያን ሳይል የአንዱን ደስታ ሌላውም አብሮ ያከብራል። ቡናውንም በጀማ እየተጠራራ፣ ከረከቦቱ ፊት እጣን ጢሱ እየተግተለተለ ጨዋታው ደርቶ ልብን ሲያሞቅ የተለየ ስሜትን የሚፈጥር ትዕይንት ነው። አንዷ ወደ ገበያ ስትሔድ ልጇን ለሌላኛዋ እመጫት ጎረቤቷ ሰጥታ የአንዷን ልጅም ሌላኛው እናት ስታጠባው አድጓል። መሶብሽ መሶቤ ነው ተባብለዋል።

ደግሞ ከልጅነት ትዝታዎቻችን ጋርም ያጋፍጠናል። ከመሀከል አንደኛው ልቦለድ የሚወለደውም ከአንቆርጫ ሰፈር ተራራ ላይ ይሆንና ወደዚያው ይዞን ይነጉዳል። የአንቆርጫ ልጆች ከአንቆርጫ ተራራ ስር ተሰባስበው ... በአንቆርጫ ማኅበረሰብ ምግቦች የተገነባውን የልጅነት ጡንቻዎቻቸውን ይፈታተሻሉ። ሁሉም በተቻለው አቅም ትንፋሹን አምቆ ጡንቻውን አጠንክሮ በመወጠር ለአሸናፊነትና ለበላይነት ይታገላል። የተሸነፈውም ይኮረኮማል። ከመጽሐፉ ውስጥ ከአንደኛው ስፍራ ስንደርስም "የእነ ጋሽ ጦና ቤት ፎሰሴና ቁርጥ፣ የእነ ጋሽ ሌጋም ቤት በሶቤና ጨከቤ፣ የእነ እትየ ኪሮስ ቤት ጥህሎና አንባሻ ... የኛ ቤት መርቃ፣ የእነ ፎዚያ ቤት ሙሽባህ ከጎረቤት ወደ ጎረቤት የሚላላከው የገብሱ፣ የበቆሎው፣ የባቄላው፣ የሽንብራ ቆሎው፣ አነባበሮውና ሌሎችም... እኛ የዛሬ አበቦች የነገ ፍሬዎች ያልተጋራ ነው፣ ያልተሻማ ነው ... ጡንቻችንን ያላዋቀርንበት የምግብ ዓይነት የለም።" እያለች ደራሲዋ በገጸ ባህሪዋ አማካኝነት ትነግረናለች።


መስዋዕትነት የተከፈለበት እናትነት ... ከኢትዮጵያዊ ወግ፣ ሥርዓትና ባህል ጋር ተቆራኝቶ ልጅ ስለምን? እንዲህ ይሆናል እያለ ከዚያ ከተለመደው ሥርዓት ጋር ሲሟገትና ሲሞግትም እንመለከታለን። "አንቺን የመሰለች ሴት ጓዳ ውስጥ አስቀምጦ፣ ትምህርትሽን እንዳትጨርሺ ፍላጎትሽን፣ ርእይሽን እንዳታገኚ አድርጓል። መኖር ያለብሽን እንዳትኖሪ አድርጎሻል። እንድትኖሪ አልረዳሽም። በአጠቃላይ ... አለና ድንገት የሚቆጨውን ነገር አፈረጠው።" እናት በበኩሏ "... ከተመደበልን ኑሮ በላይ አታግዝፈኝ። መኖር ያለብኝ እንደ ባህሌ፣ ወግና ሥርዓቴ ነው አለችው።" በማለት በሁለቱ መሀከል ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ልታሳየን ትሞክራለች። በርካታ የሆኑ የኑሮ ማሰሪያዎቻችንን መሳጭ በሆነ መልኩ ታስነብበናለች። እያነበብንም የማንናፍቀውና የማናጣጥመው የሕይወት ጣእም የለም። ከገጽ ወደ ገጽ በተሸጋገርን ቁጥር ሁሉ የምናነበው የራሳችንን ሕይወትና ማንነት ነው።

ከሌላኛው ገጽና ገጽታ ውስጥ "ዱላው ቂ" የተሰኘውን አንድ ወጣ ያለ ገጸ ባህሪ እናገኛለን። ባህሪው፣ ግብሩና ማንነቱ ከአብዛኛው የተለየ ነው። ዱላው ቂ ማለት ኮራጅና ጫፍ በነካ የኩረጃ ጥበቡም እስከ ጥግ ድረስ የወጣ ተማሪ ነው። ይህች ዓለም ፍትሐዊና ሀቀኛ አይደለችምና አንዳንዴ መጥፎ በምንለው ነገር ላይ ቆመው በኑሯቸው ግን የሚያስቀና የሕይወት ከፍታ ላይ ሊቆሙ ይችላሉ።

በመጽሐፉ ውስጥ የተቀመጠው ይህ ገጸባህሪ ብዙ እይታዎቹ እኛ እውነትን ከምናይበት መነጸር በተለየ መንገድ ነው። ድርጊቶቹ ሊያስቁና ሊያዝናኑን፤ ሊያናድዱንና ብስጭት ሊያደርጉንም ይችላሉ። የባህሪው አንኳር ዘረመል በአንባቢው እይታና አስተሳሰብ አኳያ የሚገለጽም ዓይነት ነው። እንደ አንድ ጥበባዊ እይታ ግን በጣም የምንወደውና ለማንበብ የሚያስደስት መልክ አለው። የልቦለዱን ዳራ ስንመለከት በዶሳይስ ውስጥ ከሚገኙ ገጸ ባህሪያት ሁሉ "ዱላው ቂ" አንድ የተለየ ነገር አለው።

እንዲህ ዓይነት ገጸባህሪያት ከአጭር ይልቅ ለረዥም ልቦለድ ተመራጭ ናቸው። በረዥም ልቦለዶች ውስጥ የምናገኛቸው አብዛኛዎቹ መሪ ገጸባህሪያት እጅግ ሞገደኛና ከቀሪው ማኅበረሰብ ወጣ ያለ ስብዕናና አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው። በጊዜው ልክ በማይመስሉ ነገሮች ውስጥ እያለፉና ብዙዎችንም እያስቆጡ በመጨረሻም ድንቅ የሆነ አዲስ ነገር ሠርተው ያሳዩናል። ለአብነትም በዳኛቸው ወርቁ "አደፍርስ"፣ በበዓሉ ግርማ ?ኦሮማይ? ውስጥ ደግሞ "ፊያሜታ ጊላይ"ን ለማንሳት እንችላለን። ከዚህ ለየት ባለ መንገድ ደግሞ እስከመጨረሻው ድረስ እጅግ አስቀያሚና መጥፎ ሆነው በክፋታቸው ዝነኛ የሆኑ በርካታ ገጸ ባህሪያትም አሉ። ሁሉንም የሚያመሳስለው አንድ ነገር ግን በአስተሳሰብ፣ በዕውቀትና በጥበብ የተካኑ መሆናቸው ነው። ከእነዚህ አንጻርም "ዱላው ቂን"ን አንደኛውን መልክ ሰጥተን በረዥም ልቦለድ ውስጥ ብናስቀምጠው የተዋጣለት ድርሰት እንደሚሆን ጥርጥር የለውም።

ከዚህ ወደዚያ እያልን ወደ መጽሐፉ ምረቃ ዕለት ስንመለስ፤ የምረቃ ዝግጅቱ እጅግ ውብ ነበር። ከዚህ ቀደም እምብዛም ባልተለመደ መልኩ አዳዲስ ነገሮችን አሳይቶናል። ለአብነትም ብሔር ያልገታቸው የብዕር ጠብታዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ተከሽነው መቅረባቸው ነው። በአማርኛ፣ በኦሮሚኛ፣ በትግሪኛና በጉራጊኛ ቋንቋዎች ከተለያዩ ገጣሚያን አንደበት ጣፋጭ የስንኝ እንጀሪዎች ተራግፈዋል። ከአንድ መድረክ ላይ ሆኖ እንዲህ ያለውን ኢትዮጵያዊነት መመልከት እጅጉን አስደሳች ነው። በብሔራዊ ቲያትር ሙዚቀኞች ጥኡም ሙዚቃዎችም ተንጎራጉረዋል። በየዘመናቱ በብዕራቸው ትውልድና ሀገርን ሲገነቡ የነበሩና ያሉ ደራሲያንም ተገኝተው ከአዲሱ ፍሬ




ቀምሰዋል። የመጽሐፍ ምረቃው ከታሰበበት ዓላማ አንዱ እኚህኑ እንቁና አንጋፋ ደራሲያንን ስለሰጡን ሁሉ ምስጋናን ማቅረብ ነበር። እየደበዘዘ የመጣውን የመጽሐፍ ብርሃን ለመመለስ ታላላቆቹ መንገዱን የማቅናት የመጨረሻው ትልቅ ኃላፊነት ከእነርሱ እጅ ላይ ናት። ካሳለፉትና ከነበሩበት የንባብ ዘመን አንጻር የተሻለውን ለማምጣት ከእነርሱ የሚቀርብ የለም። በምረቃው ከተገኙ አንጋፋ የጥበብ ባለሙያዎች መሀከል አንዱ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ፕሬዚዳንት አበረ አዳሙ ነበር። "በማኅበራችን ውስጥ አንድ መጽሐፍ ታተመ ሲባል በቤተሰብ ውስጥ አንድ ተጨማሪ ልጅ እንደተወለደ ያህል እንቆጥርና ደስ ይለናል።" በማለት አንብ፤ የምታነበውንም እወቅ፤ አንባቢ ስንሆን በወጣ በወረደ ሁሉ አንተራመስም የሚል ሀሳብም አክሎበታል።

ለመድረኩ ቆንጆ የሀሳብ ምልከታውን ያጋራው ሌላኛው ብርቱ የብዕር ፈርጥ ኃይለ መለኮት መዋዕል ነበር። በርካታ የመጻሕፍት ደሴቶቹን በአይነት በአይነት ሰጥቶናል። አብዛኛዎቻችንም "ጉንጉን" በተሰኘው ረዥም ልቦለዱ እናውቀዋለን።

"ተጽፎላቸው መጻሕፍትን ለማይገዙ ልብ ይስጥልን ... ወጣቶችን ለማያበረታቱ ልብ ይስጥልን፤ በማንኛውም አቅጣጫ የጥበብ ሥራዎችን ለሚኮረኩሙና ለማይደግፉ ልብ ይስጥልን ... ልብ ይስጣቸው ... ብዙውን ጊዜ ከሚያሳስቡኝ ጉዳዮች አንዱ የመጽሐፍ ምረቃ ነው። ቧልትና ቀልድ ሲሆን ... እስቲ ደግሞ እንሄድና ትንሽ ተጫውተን እንምጣ የሚባልበት አካባቢ ይኼ አዳራሽ ግጥም ብሎ ሲሞላ አውቃለሁ። አንድ ደራሲ ግን ለዓመታት ያህል አስቦ፣ አሰላስሎ ጽፎ፣ ስንት መከራውንና ፍዳውን አይቶ ያሳተመውን መጽሐፍ ለማስመረቅ ግን የእርግማን ያህል ይቀራል። ... እራሳችንን ልናርምና ልንወቅስ ይገባል። ... ደራሲ ጽፎ እንጂ አትርፎ አያውቅም። ሕዝብ በአክብሮት ተጠርቶ ሳይመጣ መቅረት ማለት የደራሲያኑ ጉድለት ሳይሆን የማኅበረሰቡ የሀፍረት ማቅ ነው።" ሲል ነበር ያሳሰበውን የመጻሕፍቱን ዓለም ሰቆቃ ይገለጸው። ደራሲ ኃይለመለኮት "ዶሳይስ"ን በተመለከት ጠለቅ ያለ ሙያዊ አስተያየቱን ባያጋራም እንደ አንድ አንባቢ በብዙ ጉዳዮች የተሻለ መጽሐፍ ስለመሆኑ አንስቷል።

ጸሀፊ ተውኔትና ባለቅኔ አያልነህ ሙላት እንዲህ ባሉ ስፍራዎች ላይ እየተገኙ ለጥበብ የሚገባትን፣ ሙያውም የሚወደውን ነገር በመስጠት ደረጃ ምናልባትም ከአንጋፋዎቹ ግንባር ቀደም ነው ለማለት ይቻላል። የደራሲያኑን አዳዲስ የመጻሕፍት ሥራዎቻቸውን አስቀድሞ በመመልከትና ሙያዊ አስተያየቱን ለማጋራትም የሚቀድመው ያለ አይመስለኝም። እሱም ገና ወደ መድረኩ ሲወጣ "መጽሐፉን ግን ከሁላችሁም በፊት አግኝቼ ተመልክቼው ነበር፤ ኃይለመኮት እንኳን ሁል ጊዜም እኔን ቀዳሚ እርሱ ነው" ሲል በጨዋታ መልክ ቢያነሳትም፤ ከዚህ ረገድ ትልቁን ምስጋና ሊቸር ይገባዋል። በ"ዶሳይስ" የመጽሐፍ ሽፋን ላይም ምልከታውን አኑሮበታል።

"እኔ እንኳን ስጠራ መጽሐፉን ትመርቃለህ ተብዬ ነውና የሽማግሌ ምርቃት እመርቃለሁ ... ከምንም በላይ ዛሬ እዚህ መድረክ ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የቀረበውን ግጥም ስሰማ እጅግ ደስ ብሎኛል። ኪነ ጥበብ የሚያድገው እንደዚህ ነው። ... ፖለቲካ አይደለም ሕዝብን ከህዝብ ሊያገናኝ፤ ሊያቀራርብ የሚችለው። እንደዚህ አይነት የጥበብ ሥራዎች ናቸው። ዛሬ የተመለከትነው ነገር ነገ መቀጥል ያለበት ጥሩ ጅምር ነው። አስቀጥለንም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወርን፤ እንዲህ እያሰባጠርን ብናቀርብ ኪነጥበብ የማይቀርፈው የለምና ብዙ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ የምንችል ይመስለኛል።" በማለት ገዘፍ ያለውን ልባዊ ምስጋናውን ለኩሪ ቸሯታል። ይህ የአንባቢያንና የመጻሕፍት ጉዳይ ግን አያልነህ ሙላትን ጨምሮ ሁሉንም ያሳሰበ ጉዳይ ነበር።

በነበረው የምረቃ ስነስርዓት ወቅት ደራሲዋ አንድ ቅር ያሰኛት ጉዳይ ነበር። ቀደም ሲል ከኪነጥበብ ሰዎች ባሻገር የትምህርት ቤት የኪነጥበብ አባላት፣ ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆችም ጭምር በመጽሐፍ ምረቃው ላይ እንደሚገኙ ነበር። ዝግጅቱም ሆነ የጥሪ ካርዱም ረዘም ላለ ጊዜ የተሰናዳው በዚሁ መልክ ነበር። ነገር ግን ለምረቃው ሦስት ቀናት ብቻ ሲቀሩት የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በዝግጅቱ ላይ ሊገኝ እንደማይችል ከትምህርት አስተዳደሩ ለደራሲዋ ተገለጸላት። የእነርሱ የመገኘት ጉዳይ ታዳሚው እንዲበረከት፣ ለጊዜያዊ ድምቀትና ለግርግሩ አልነበረም። ከላይ እንደተመለከትነውም አንጋፋዎቹን ጨምሮ የሁሉም ጭንቀት የነበረው የትውልዱ ከመጽሐፍ ዓለም ተሰዶ በንባብ ላይ ማፈንገጡ ነው። ለዕለቱ ታስቦ የነበረው አቢይ ጉዳይ "ዶሳይስ"ን ማስመረቅ ብቻ ሳይሆን የተጋረጠውን ችግር ለመቅረፍ አንድ እርምጃ ትውልዱን የማቅናት ሀሳብም የያዘ ነበር። ደራሲና ገጣሚ ኩሪ አየለ ደግሞ በተለየ መንገድ ከትምህርትና ተማሪዎች ጋር ቅርበት ያላት ናት። ጥቂት ለማይባሉ ዓመታት በመምህርነት አገልግላለች። በተለያዩ የመማሪያ መጻሕፍቶች ውስጥ ግጥሞቿ በማስተማሪያነት ተካተዋል። ለዚህም ነው የንባቡን ጎጆ ለማቅናት ከየቱ ጋር መጀመር እንዳለባት ተረድታ እንዲገኙ ጥሪ ማቅረቧ። እናም በዚህ ዝግጅት ላይ ተማሪዎቹ ለመገኘት እንደማይችሉ በተነገራት ጊዜ ግራ በመጋባት ለምን? ስትል ጠየቀች። "ምክንያቱም የኛ ተማሪዎች የማንበብ ችግር የለባቸውም። ባይሆን ሌሎች ያለባቸውን ..." የሚል ምላሽ እንደተሰጣት ኩሪ ተናገረች። ነገሩ የሚያስገርም ነው፤ አለመገኘታቸው ሳይሆን ምላሹ ... ከአንድ ትውልድን ለመገንባት ከሚሠራ አካል እንዲህ ያለውን ምላሽ መስማት ለጆሮም ሰቅጣጭ ነው። ለፈተናው ብቻ የሚጠቅመውን መደመርና መቀነስን ብቻ እያነበበ የኖረ ተማሪ ነገ ላይ እንዴት ያለው ትውልድ ነው የሚሆነው?

መጽሐፍ ሲባል የሚጠራው ብዙ፤ የሚገኘው ግን ጥቂት አይሁን። የኋላ ኋላ የጥበብ ቀንዳችን ታጥፎና ቁልቁል ተጠማዞ ወደ ከፋው እንዳንገባም እናስብ፤ እናሰላስል።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ልዩ ፍላጎትን በአካቶ


አስናቀ ፀጋዬ

ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩና የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ባደጉት ሀገራት ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር አይቸገሩም:: ክህሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ፣ ለእነርሱ ተብለው የተዘጋጁ ማዕከላት ከመኖራቸው ባሻገር በመደበኛው ሥርዓተ ትምህርትም ታቅፈው ለመማር የሚያስችላቸው ቅድመ ሁኔታዎች ተመቻችተውላቸዋል:: ከዚህ በተቃራኒ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ገና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሚገኙ ከኦቲዝም ጋር የሚኖሩና የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች የሚማሩባቸውና ክህሎቶችን የሚያዳብሩባቸው ለእነርሱ ተብለው የተዘጋጁ ማዕከላት እምብዛም የሉም::

ያሉት ማዕከላት የተገነቡት ልጆቻቸው በዚሁ ችግር ምክንያት ተጠቂ በሆኑ ወላጆች አማካኝነት ነው:: ልጆቹ በነዚህ ማዕከላት የመግባት እድል ቢያጋጥማቸው እንኳን የመግባባት፣ የንግግር፣ ራስን የመቆጣጠርና ሌሎችንም ክህሎቶችንና እውቀቶችን ካገኙ በኋላ ወደ መደበኛው ትምህርት ለመቀላቀል ችግር ሲገጥማቸው ይታያል:: ይህ ችግር ደግሞ በአብዛኛው መደበኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ልጆቹን ለመቀበል ፍቃደኛ ካለመሆን ይመነጫል። በዚህም ምክንያት በርካታ ወላጆች ልጆቻቸውን የኦቲዝምና የአዕምሮ እድገት ውስንነት መንከባከቢያ ማዕከላት ካቆዩ በኋላ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ለማስገባት ሲቸገሩ ይስተዋላል::

መንግሥት የልዩ ፍላጎት አካቶ ትምህርትን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ሰንበት ብሏል:: የመንግሥት ትምህርት ቤቶችም ይህን ፕሮግራም ተቀብለው ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ:: ይሁንና ይህ የልዩ ፍላጎት አካቶ ትምህርት በግል ትምህርት ቤቶች በኩል እምብዛም ሲሰጥ አይታይም:: ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ የግል ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ተቀብለው በማስተማር ለሌሎች ትምህርት ቤቶች አርዓያ ለመሆን በቅተዋል::

ወይዘሮ ማርታ ተሾመ ባምላክ ተስፋዬ የሚባል የሰባት ዓመት ልጅ አላቸው:: ባምላክን ወደ ትምህርት ቤት የላኩት የአራት ዓመት ልጅ ሳለ ነበር:: ነገር ግን የጤና ችግር እንዳለበት ያወቁት ዘግይተው ነው:: ሁሌም ትምህርት ቤት ይጠራሉ:: በራሱ መፀዳዳት እንደማይችልም ይነገራቸዋል:: ችግሩ እንዳለ



ወይዘሮ ማርታ ተሾመ



ወይዘሮ ሰርክአዲስ አየለ



ወይዘሮ ሀድራ ሰይድ

ሆኖ ባምላክ ለስድስት ወራት በትምህርቱ ዘለቀ:: በኋላ ላይ ወይዘሮ ማርታ ትምህርቱን አቋርጠው ሐኪም ቤት ወስደውት ከኦቲዝም ጋር እንደሚኖር አረጋገጡ:: ከዛ በኋላ ልጃቸው ቴራፒ እንዲያገኝ በብዙ ለፍተዋል::

በትርፍ ጊዜ እቤት መጥቶ የሚረዳ ሰው ሲያገኙ ቀደም ሲል የማያወራው ልጃቸው አባባ .. እማማ ማለት ጀመረ:: ተረጋጋ፣ ኤ ቢ ሲ ዲ ፨ ፨ ፨ በደምብ አወቀ:: ወይዘሮ ማርታ እንደገና ሌላ ትምህርት ቤት ባምላክን ለማስገባት ቢፈልጉም አንድም ትምህርት ቤት ሊቀበሏቸው አልቻሉም:: አንድ ዓመት የቴራፒ ማዕከል እንዲቆይ ካደረጉ በኋላ ልጃቸውን ተቀብሎ የሚያስተምር ትምህርት ቤት አገኙ:: ዛሬ ባምላክ ወደ አጋቶስ አካዳሚ ከመጣ በኋላ ምንም እንኳን በትምህርት አቀባበል በኩል ችግር የሌለበት ቢሆንም የባሕሪ መለዋወጥና ችግሮችን መቅረፍ ችሏል:: ትምህርቱ ላይም ይበልጥ በርትቷል:: በራሱ መፀዳዳት ችሏል:: ከተማሪዎች ጋርም ተግባብቶ መጫወትና መማር ይችላል::

የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በመደበኛ ትምህርት አካቶ የማስተማሩ ሁኔታ በተለይ በግል ትምህርት ቤቶች እምብዛም እንደማይታይ የሚገልፁት ወይዘሮ ማርታ ኦቲዝምና የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ቁጥር እየጨመረ እንደመምጣቱ ትምህርት ቤቶች በራቸውን ክፍት አድርገው መቀበል አለባቸው ይላሉ:: እነዚህ ልጆች ሁሉንም ነገር ማግኘት ይገባቸዋልና ትምህርት ቤቶች ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ይበልጥ ትኩረት በመስጠት በመደበኛው ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ሊያግዟቸው እንደሚገባም ይጠቁማሉ::

ወይዘሮ ሰርክአዲስ አየለ በአዲስ አበባ ሰሜን ማዘጋጃ አካባቢ ነዋሪ ናቸው:: የአስራ አራት ዓመት ሴት ልጃቸው ከኦቲዝም ጋር ትኖራለች:: ከዚህ ቀደም ሌላ ቦታ ልጃቸውን ለማስተማር ሞክረው ብዙ ሳትቆይ ነው ያስናበቷት:: ልጃቸው አጋቶስ አካዳሚ ከገባች በኋላ ተረጋግታለች:: አፏንም ፈታለች:: በትምህርቷም ጎብዛለች:: ዘንድሮ ኬጂ 3ን አጠናቃለች:: ይህን ለውጥ ማምጣት የቻለችው አካዳሚው ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ትኩረት ሰጥቶና ከሌሎች መደበኛ ተማሪዎች ጋር ቀላቅሎ በማስተማሩ ነው:: በተጨማሪም ትምህርት ቤቱ ልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን መሠረት ያደረጉ ትምህርቶችን በመስጠቱም ነው ልጃቸው ለውጥ ልታመጣ የቻለችው::

አሁን የወይዘሮ ሰርክአዲስ ስጋት ልጃቸው ኬጂ 3 ካጠናቀቀች በኋላ በቀጣይ አንደኛ ክፍል የት ትምህርት ቤት እንደሚያስገቧት ነው:: ምክንያቱ ደግሞ አብዛኛዎቹ ከአንደኛ ደረጃ አንደኛ ክፍል በኋላ የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ተቀብለው ስለማያስተምሩ ነው:: በዚህ አጋጣሚ ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ተቀብለው እንዲያስተምሩ ይጠይቃሉ:: መንግሥትም የልዩ ፍላጎት ትምህርት በግል ትምህርት ቤቶችም ጭምር እንዲሰጥ ማድረግ እንዳለበት ይጠቁማሉ::

ወይዘሮ ሀድራ ሰይድ የአጋቶስ አካዳሚ ልዩ ፍላጎት ትምህርት አስተባባሪ ናቸው። እርሳቸውም ከኦቲዝም ጋር የሚኖር የአስራ አራት ዓመት ልጅ አላቸው:: ከዚህ ቀደም በነህሚያ የኦቲዝም ማዕከል ልጃቸውን አቆይተዋል:: በማዕከሉም ከኦቲዝም ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሥልጠናዎችን ወስደዋል:: ከዛ ማዕከል ከወጡ በኋላ ደግሞ ልጃቸውን በአጋቶስ አካዳሚ እያስተማሩና በኦቲዝም ዙሪያ ለመምህራን ሥልጠና እየሰጡና እያበቁ ልጃቸውን ሦስት ዓመት አስተምረው ለአንደኛ የክፍል ደረጃ አብቅተዋል::

እርሳቸው እንደሚሉት ትምህርት ቤቱ አስረኛ ዓመቱን ይዟል:: በሩን ክፍት አድርጎ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ተቀብሏል:: ከዚህ በተቃራኒ ግን ሌሎች ትምህርት ቤቶች ይህን አያደርጉም:: በዘንድሮ ዓመትም 29 የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ተቀብሎ አስተምሯል:: የንግግር ቴራፒ መምህርትም ቀጥሮ በሳምንት ሁለት ግዜ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች እንዲማሩ ተደርጓል:: ነህሚያ ኦቲዝም ማዕከልም ለመምህራን በኦቲዝም ዙሪያ ሥልጠና ሰጥቷል:: በመደበኛነት ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ልጆችም ከልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ጋር አብረው በመዋላቸው የተለያዩ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ እገዛ አድርገዋል::

በዚህም ከመደበኛ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ የተደረጉት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ሀሳባቸውን የመግለፅ፣ የማውራት፣ ጉዳት ሊደርስባቸው ሲል የመናገርና ሌሎችንም ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ አስችሏቸዋል:: ወላጆችም ከኦቲዝም ጋር በተያያዘ ግንዛቤው እንዲኖራቸው ተደርጓል:: በዚህም ሌሎች ወላጆች ይህን ሰምተው ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤቱ እስከመላክ ደርሰዋል:: ይሁንና ልጆቹ በቀጣይ የአንደኛ ክፍል ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ትምህርት ቤቶች በራቸውን ክፍት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ለዚህ ደግሞ መንግሥት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል::

# ዓለም አቀፍ

## የጋዛው ጦርነት የሚቆም ከሆነ ሄዝቦላ በእሥራኤል ላይ ጥቃት መሰንዘሩን እንደሚያቆም አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የጋዛው ጦርነት የሚቆም ከሆነ ሄዝቦላ በእሥራኤል ላይ ጥቃት መሰንዘሩን እንደሚያቆም አስታወቀ፡፡

የቡድኑ ምክትል መሪ ሼክ ናይም ካሲም “በግጭቱ የተሳተፍነው ለሀማስ እና ለፍልስጤማውያን ያለንን አጋርነት ለማሳየት ነው፤ እሥራኤል ውጊያውን የምታቆም ከሆነ ያለምንም ውይይት እኛም ጥቃት ማድረሳችን እናቆማለን” ብለዋል፡፡

እሥራኤል በጋዛ የምድር ውጊያ ከጀመረች ከባድ ዋጋ ትከፍላለች - ሄዝቦላህ

ከአሶሼትድ ፕሬስ ጋር ለ40 ደቂቃ ያክል ቃለ ምልልስ ያደረጉት የቡድኑ ምክትል መሪ እሥራኤል በጋዛ የምታካሂደውን ፍትሐዊ ያልሆነ ጦርነት የምትቀጥል ከሆነ በሊባኖስ እና እሥራኤል ድንበር ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት አትችልም ሲሉ ዝተዋል፡፡

ባለፈው ወር የእሥራኤል መከላከያ በሊባኖስ ሙሉ ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችል ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ማጠናቀቁን ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡

ይህን አስመልክቶ ምላሽ የሰጡት የሄዝቦላ ምክትል መሪ ሼክ ካሲም እስራኤል በሄዝቦላ ላይ ሙሉ ጦርነት የማወጅ አቅም የላትም ብለዋል፡፡

የተገደበ ጦርነት አደርጋለሁ በሚል በሊባኖስ ድንበር ውስጥ ገብታ የምትንቀሳቀስ ከሆነ ደግሞ ጦርነቱን ወደግዛቷ እንደምወስደው ልታውቅ ይገባል ነው ያሉት፡፡

እሥራኤል ሙሉ ጦርነት የምታወጅ ከሆነ በጦርነቱ እነማን ሊሳተፉ እንደሚችሉ መቆጣጠር አትችልም ሲሉ የግጭቱ መጠን ሊሰፋ እንደሚችልም አስጠንቅቀዋል፡፡

የሄዝቦላ አጋር ናቸው የሚባሉ በመካከለኛው ምሥራቅ የሚንቀሳቀሰው አክሲስ የተሰኘው ታጣቂ ቡድን እንዲሁም በኢራቅ ፣ በሶሪያ እና የመን ያሉ ተዋጊዎች ኢራንን ጨምሮ በዚህ ጦርነት ሊሳተፉ እንደሚችል ስጋት አለ፡፡

ቴልአቪቭ በጋዛ ጦርነት ካወጀች አንስቶ ላለፉት 9 ወራት ከእሥራኤል ጋር በተካረረ ውጥረት ውስጥ የሚገኘው ሄዝቦላ ለሃማስ ያለውን ድጋፍ ለማሳየት በእሥራኤል ላይ የተለያዩ የሮኬት እና የድሮን ጥቃቶችን ሰንዝሯል፡፡



ሁለቱ አካላት የሚገኙበት ሁኔታ ወደ ለየለት ጦርነት ተቀይሮ ቀጣናዊ ግጭትን እንዳያስከትል ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ስጋቱን እየገለጸ ይገኛል፡፡

ሆኖም ሁለቱም አካላት እርስ በእርስ የሚሰጧቸው መግለጫዎች እና ወታደራዊ ዝግጅቶች የጦርነቱን አይቀሬነት የሚያሳብቁ ናቸው ያሉ ተንታኞች ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በመተንተን ላይ ናቸው፡፡

በእሥራኤል እና ሄዝቦላ መካከል ዝቅተኛ ነው በሚባለው አሁን ባለው ግጭት በሁለቱም ወገን ድንበር ላይ የሚኖሩ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ ንጹሐን ሲፈናቀሉ በሊባኖስ በኩል 450 ንጹሐን ሰዎች እና ታጣቂዎች ተገድለዋል በእሥራኤል በኩል ደግሞ 16 ወታደሮች እና 11 ንጹሐን ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡

ሀማስ በጋዛ ያለው ጦርነት እንዲቆም እና ስምምነት ላይ እንዲደረስ ፍላጎት ያለው ሲሆን ለዚህም ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በእሥራኤል ላይ ጫና እንዲያሳድር በመጠየቅ ላይ ይገኛል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ በበኩላቸው የሀማስ ወታደራዊ እና የአስተዳደር አቅም ሳይበታተን የጋዛው ጦርነት አይቆምም በሚለው አቋማቸው ጸንተዋል፡፡

የሊባኖሱ ሄዝቦላህ እሥራኤል በጋዛ የምድር ውጊያ ከጀመረች ከባድ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል ማለቱ የሚታወስ ነው።

የቡድኑ ምክትል መሪ ሼክ ናይም ካሴም ማስጠንቀቂያ የተሰማው የእሥራኤል ጦር በደቡባዊ ሊባኖስ በፈጸመው ጥቃት ስድስት የሄዝቦላህ ተዋጊዎች በተገደሉበት በትናንትናው እለት ነው።

“የእሥራኤልን ጦር ለማዳከም ጥረት እያደረግን ነው፤ ዝግጅታችን ምን እንደሚመስልም አሳይተናቸዋል” ብለዋል ምክትል መሪው።

በኢራን የሚደገፈውና በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ሮኬቶች፣ ሚሳኤሎች እና የተለያዩ ድሮኖች የታጠቀው ሄዝቦላህ በሰሜናዊ እሥራኤል አዲስ የጦር ግንባር እንደከፈተ ይታወቃል።

እሥራኤልም በድንበር ላይ በርካታ ታንኮች እና ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ተክላለች። የእሣራኤልና ሃማስ ጦርነት ከተጀመረ አንስቶ ለፍልስጤሙ ቡድን አጋርነቱን ያሳየው ሄዝቦላህ በየቀኑ ወደ እሥራኤል ሮኬቶችን ከመተኮስ አላረፈም።

# ስፖርት



## ለአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ውጤታማነት ትኩረት ተሰጥቷል

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ወጣቶች አትሌቲክስ ሻምፒዮና በሃዋሳ ከተማ መካሄድ ከጀመረ ዛሬ ሦስተኛ ቀኑን አስቆጥሯል፡፡ በሁሉም የሩጫና የሜዳ ተግባራት ወጣት አትሌቶችን የሚያፎካክረው ውድድሩ ከክልሎች እና ክለቦች የተወጣጡ በርካታ አትሌቶችን በማሳተፍ ላይም ነው፡፡

ለ12ኛ ጊዜ የሚካሄደው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከትላንት በስቲያ በደማቅ ሁኔታ የተጀመረ ሲሆን፤ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ተተኪ አትሌቶች የማጣሪያና የፍጻሜ ውድድራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው። ሻምፒዮናው ተተኪ አትሌቶች እርስ በእርስ እንዲፎካከሩ፤ እንዲሁም ሀገርን መወከል የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመቻች ከመሆኑም ባለፈ ለአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት አትሌቶች ትርጉሙ የተለየ ይሆናል።



እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በእነዚህ የአትሌቲክስ ዘርፎች በአሕጉር አቀፍ ደረጃ ከተሳትፎ የዘለለ የውጤት ታሪክ የላትም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፌዴሬሽኑ በሰጠው ትኩረት በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮናም ጭምር በመሳተፍ የውጤት ፍንጭ ታይቶበታል። ይኸውም ወጣቶች በተነቃቃ መልኩ ውድድራቸውን እንዲያከናውኑ የሞራል ስንቅ እንደሆናቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም አጠናክሮ ለማስቀጠል ከአትሌቲክሱ ባለድርሻዎች ጋር ጠንክሮ በልዩ ሁኔታ እንደሚሠራ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ባልተለመደ ሁኔታ የአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት አትሌቶችን በስፋት አካታ የተሳተፈች ሲሆን፤ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴና ውጤት በማስመዝገብ ውድድሯን አጠናቃለች። ከፍተኛ በጀት ተመድቦ የአጭርና የሜዳ ተግባራት አትሌቶችን ያሳተፈው ትልቁ የአሕጉሪቱ መድረክ በዘርፉ ላሉ አትሌቶች ተስፋን የሰጠ ነው። በመሆኑም በትኩረት ከተሠራ ኢትዮጵያ በእነዚህ የአትሌቲክስ ዘርፎችም ውጤት የምታስመዘግብበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አመላክቷል።

ወጣቶች የሚሳተፉባቸው ይህንን መሰል ሻምፒዮናዎች ደግሞ ብዙም የውጪ የውድድር ዕድልን ለማያገኙት የአጭርና የሜዳ ተግባራት አትሌቶች ዕድሉን በማመቻቸት እና ራሳቸውን እንዲያሳዩ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የሲዳማ ቡናው የዝላይ አሠልጣኝ አባንግ ኮድ ይሄንኑ የሚያጠናክር ሃሳቡን አንጸባርቋል።

ዘንድሮ በአጭርና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች የተሰጠው ትኩረት የተሻለ መሆኑንና ለአትሌቶቹ መነቃቃትን ፈጥሯል። በተለይ በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ብዙ የአጭርና ሜዳ ተግባራት አትሌቶች ተሳትፎ ያሳዩት እንቅስቃሴ ተስፋ ሰጪ ነበር። አሠልጣኙ እንደ ልምድ ከወሰዳቸው ጉዳዮች መካከል የአመጋገብ እና የሥልጠና አሰጣጥ ላይ ብዙ ነገሮች መሻሻል ይኖርባቸዋል። በመሆኑም አሠልጣኞች የማነቃቂያ ሥልጠናዎችን እንዲወስዱ በማድረግ በዘርፉ ውጤት እንዲመጣ ማድረግ ይገባል።

ከዚህ ቀደም በእነዚህ ውድድሮች የነበረው ተሳትፎ ጥሩ የነበረ ቢሆንም በመሐል ተቀዛቅዞ ዘንድሮ በተሰጠው ትኩረት ዳግም ጥሩ ተሳትፎን ማድረግ ተችሏል።

ጋና እና ካሜሮን በተደረጉት ውድድሮች በዝላይ፣ ውርወራና አጭር ርቀት ሩጫ የተገኘው ውጤት ተስፋ ሰጪ ሲሆን፤ የሥልጠና ሂደትና የአመጋገብ ሥርዓትን በማስተካከል ውጤታማ አትሌቶችን ማፍራት እንደሚቻል ያመላከተም ነው።

በአሕጉር አቀፉ ውድድር በርዝመት ዝላይ እና ከፍታ ዝላይ ላይ ተመዝግቦ የነበረው የኢትዮጵያ ክብረወሰን የተሻሻለ ሲሆን፤ በሃገር ውስጥ ግን ባለው የልምምድ ቁሳቁስ እጥረት ምክንያት ክብረወሰን ማሻሻል አስቸጋሪ ነበር። ከዓለምና ከአፍሪካ ጋር ያለው ልዩነት ጥቂት በመሆኑ ከዚህ በተሻለ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ከሆነ በአጭር ጊዜ በአጭርና ሜዳ ተግባራት ውድድሮች ውጤት ሊመዘገብ ይችላል። ለዚህም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የውድድር ዕድሎችን እንዲያሰፋና ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮችም ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንደሚኖርባቸውም ጠቁሟል።

ለስፖርተኞቹ የሚያስፈልገው ድጋፍ በሙሉ የሚደረግ ከሆነም ውጤታማ በመሆን የማናጀሮችን ቀልብ መሳብ ይቻላል፡፡ በየክልሉ የውድድር እድሎችን በማስፋት ስፖርተኞች ወጥ በሆነ አቋም እንዲቀጥሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ማበረታታትም ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ በበኩላቸው፤ በ23ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና በርካታ የአጭርና የሜዳ ተግባራት አትሌቶች መሳተፋቸው የሞራል መነሳሳት እንደፈጠረባቸው ገልጸዋል። ፌዴሬሽኑ አሠልጣኞችንም እያበረታታ በመሆኑ በቀጣይ ጠንክረው በመሥራት በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ለመሆን በሚያስችል ሁኔታ ውድድራቸውን እያካሄዱ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

ፌዴሬሽኑ አሠልጣኞችን ወደ ውጪ በመላክና ዓለም አቀፍ የዘርፉ ባለሙያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በመጋበዝ ሥልጠና እንዲወስዱ አድርጓል። ለክለቦችና ለክልሎች የሥልጠና ድጋፍን፣ ለፕሮጀክቶችና ማዕከላት የትጥቅ፣ የአሠልጣኞችን ደመወዝ እና የአትሌቶች የላብ መተኪያ ድጋፍንም ያደርጋል። ሁሉም የድርሻውን ወስዶ ጠንክሮ በመሥራትና ፌዴሬሽኑ የተለመደውን ድጋፍ በማስቀጠል በአጭርና የሜዳ ተግባራት ውጤት ለማምጣት እንደሚሠራም ጠቁመዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## ከባለድርሻ አካላት አድናቆት የተሰጠው ቅንጅታዊ ሥራ

**ስሜነህ ደስታ**

የአዲስ አበባ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የ2016 ዓ.ም. በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸምን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ሰሞኑን በጌት ፋም ሆቴል በመገናኘት ገምግሟል። በዕለቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የተሠሩ ሥራዎችን ለመገምገም የአዲስ አበባ ምክር ቤት የሠላምና ፍትሕ መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ መሐመድ ገልማ (ዶ/ር)፣ የባለድርሻ አካላት የቢሮ ኃላፊዎችና ተወካዮች እንዲሁም የደንብ ማስከበር ባለሥልጣኑ አመራሮች ተገኝተዋል፡፡



መድረኩን የመሩት



ተሳታፊዎች

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ፤ በባለድርሻ አካላት ትብብር በደንብ ጥሰት ቅድመ መከላከል ተግባር አበረታች ውጤት እየተገኘ መሆኑን ገልጸዋል። በመሬት ወራራና የጎዳና ንግድ፣ በሕገ-ወጥ ግንባታና የእንስሳት እርድ እንዲሁም አዋኪ ተግባራትን በመከላከል ረገድ የተሳካ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል፡፡ አያይዘውም ከተማዋን ውብ፣ ፅዱ እና ማራኪ ለማድረግ እንዲሁም የሕዝብ ሀብት የሆነውን መሬት ከመጠበቅ አንፃር በዘንድሮ ዓመት በርካታ ውጤታማ ሥራዎች እንደተሠሩ ገልፀዋል።

ከሥራ አስኪያጁ መክፈቻ ንግግር በኋላ የባለሥልጣኑ የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ቀፀላ ከሃያ ሦስቱ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተሠሩ ሥራዎችን ለብቻ ለብቻ በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ በዚህም ከአስራ አምስቱ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ተባብረው መንቀሳቀስ የቻሉ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም ከአራት ተቋማት ጋር በነበረው የሥራ እንቅስቃሴ ተቋማቱ ባሳዩት የመተባበር እንቅስቃሴ መካከለኛ ደረጃ ላይ ያሉ መሆኑን አንስተዋል፡፡ አራት ተቋማት ደግሞ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ ያሉ መሆኑን ከተሠራው የቅንጅት ሥራ አኳያ በማንሳት ለውይይት የሚያግዝ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡

ከዚያም የአዲስ አበባ ምክር ቤት የሠላምና ፍትሕ መልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ መሐመድ ገልማ (ዶ/ር) እና የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ መድረኩን እየመሩ፣ ባለድርሻ አካላት ከቀረበው ሪፖርት በመነሳት ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

በመጀመሪያ ሀሳባቸውን የሰጡት ከአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ ቢሮ የመጡት አቶ ኤልያስ መሐመድ ናቸው፡፡ እሳቸውም ባለሥልጣኑ ከደንብ ጥሰት ባሻገር የሕዝቡ ሠላም እንዲጠበቅ ከሠላምና ፀጥታ፣ ከፖሊስ እና ከሌሎች የፀጥታ አባላት ዘንድ በመተባበር ሽፍት እስከማጠፍ ደረጃ በመድረስ የሠራቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉ እኛ ምስክሮች ነን በማለት ከባለድርሻ አካላት ጋር ተሠሩ ተብለው ለቀረቡ ሥራዎች እውቅና ሰጥተዋል፡፡ አያይዘውም ባለሥልጣኑ በቀጣይ ትስስሩን በማጠናከርና በማስፋት መትጋት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

ሌላው ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት የመጡት አቶ አታክልቲ ገብረሚካኤል የዘንድሮን የባለሥልጣኑን ቅንጅታዊ አሠራር በእጅጉ አድንቀው፣ የቅንጅታዊ ሥራው አፈጻጸም ከክፍለ ከተማ-ክፍለ ከተማ እንዲሁም ከወረዳ-ወረዳ የሚለያይ ስለሆነ በሁሉም ክፍለ ከተማና ወረዳ ወጥ የሆነ የቅንጅት ሥራ እንዲሠራ አሳስበዋል፡፡

በመቀጠል ከአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የመጡት ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ ሎካ ዳለቻ እንዳሉት ቀደም ሲል በኮሚሽኑና በባለሥልጣኑ ዘንድ የመገፋፋት ሁኔታ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው፣ በ2016 ዓ.ም. ግን እስከታችኛው ፈጻሚ ድረስ በመነጋገር በተሠራው ቅንጅታዊ ሥራ በጣም የምንኮራ ከመሆኑ በላይ ለባለሥልጣኑ ትልቅ ምስጋና እንዲሁም ክብር እንሰጣለን ብለዋል፡፡

በክትትል ሥራው የተሳተፉት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት የመጡት ደግሞ ባለሥልጣኑ ምን አቅዶ፣ ምንያህል ተግብሯል የሚለውን ለማየት በከተማ (በማዕከል) ደረጃ ብቻ ሳይሆን እታች ድረስ ሄደን ባየነው በቂርቆስ ክፍለ ከተማም ይሄው የቅንጅት ሥራ መቀጠሉን አስተውለናል ብለዋል፡፡ ሌሎቹም ተሳታፊዎች የባለሥልጣኑን ቅንጅታዊ ሥራ አድንቀው ተናግረዋል፤ ይበጃል ያሉትን ሀሳብም ሰጥተዋል፤ እንዲሁም ቅንጅታዊው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል፡፡

በመጨረሻም በተከበሩ መሐመድ ገልማ (ዶ/ር) እንዲሁም በባለሥልጣኑ አመራሮች ከባለድርሻ አካላት ለተነሱ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ በማጠቃለያውም በመሐመድ (ዶ/ር) የቀጣይ የሥራ አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡